# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐቡሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## በከተማ ልማት፣ ቤቶች እና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የከተማ ፕላን ምንጭ፣ ዝግጅት እና አፈጻጸምን አስመልክቶ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ሚያዚያ 2007
አዲስ አበባ

## ማውጫ


ክፍል አንድ .................................................. 1

መግቢያ .................................................. 1

የከተሞች ፕላን ኢንስቲትዩት አመሰራረት፤ .................................................. 2

የሚኒስቴር መ/ቤቱ አመሰራረት .................................................. 3

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ራዕይ፣ ዓላማ፣ .................................................. 3

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥልጣንና ተግባር .................................................. 4

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል፤ .................................................. 5

የፋይናንስ ምንጭ፤ .................................................. 6

የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ .................................................. 6

የኦዲቱ አካባቢ .................................................. 7

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫ (audit issue) እና የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria)፣ ....... 7

የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ .................................................. 8

የሥራ ሂደት መግለጫ (process description) .................................................. 10

በከተማ ፕላን የሬጉላተሪና ድጋፍ አሰጣጥ ረገድ የጥናትና ምርምር የስራ ፍሰት .................. 10

በከተማ ፕላን የሬጉላተሪና ድጋፍ አሰጣጥ ረገድ የስልጠና የስራ ፍሰት .................................................. 11

በከተማ ፕላን የሬጉላተሪና ድጋፍ አሰጣጥ ረገድ የክትትልና ግምገም የስራ ፍሰት ................ 12

ክፍል ሁለት .................................................. 13

ግኝቶች .................................................. 13

2.1 የከተሞችን ፕላን ምንጭ እና ዝግጅት ቀልጣፋና እና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ፤ ................. 13

ብሔራዊ የከተማ ልማት አቅድ (National Urban development scheme) መዘጋጀቱን በተመለከተ .................................................. 13

ክልላዊ የከተማ ዕቅድ/ፕላን መዘጋጀቱን በተመለከተ .................................................. 14

በከተማ ፕላን ዝግጅት ወቅት የሚመለከታቸው አካላት ተሳትፎን በተመለከተ .................................................. 14

ከተማን ለማደስ ምቹ የመኖሪያና የሥራ አካባቢ ለመፍጠር የሚያስችል እቅድ ስለመዘጋጀቱ፤.. 16

የአካባቢ ልማት ፕላን በሚመለከተው አካል ጸድቆ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ .............. 17

2.2 የከተማ ፕላንን በሚመለከት የሚደረገው የቴክኒክ እና የአቅም ግንባታ ድጋፍ ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና እና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ፤ .................................................. 18

የቴክኒክና የአቅም ግንባታ ድጋፍ የአሰራር ማንዋል ዝግጅትን በተመለከተ .................................................. 18

የጥናት ሰነዶች በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን በተመለከተ ........................................ 19

2.3 የከተሞች ፕላን አፈጻጸም የቁጥጥር፣ክትትልና ግምገማ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤ ........................................................................................ 20

ማንኛውም የጸደቀ ፕላን በሚተገበርበት ወቅት የፕላን ጥሰት እንዳይኖር ክትትልና ቁጥጥር መደረጉን በተመለከተ ........................................................................ 20

የከተማ ፕላን ዝግጅትና አፈፃፀም የክትትልና የግምገማ ማንዋልና መስፈርትን በተመለከተ..... 22

የክትትልና የግምገማ ሪፖርት ግበረ-መልስና የተወሰደ እርምጃን በተመለከተ ...................... 23

2.4 የከተማ ፕላን አፈጻጸምን በተመለከተ ቅንጅታዊ አሰራር እና የመረጃ ልውውጥ ተግባር ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና እና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ፤ .................................................................. 24

ከከተማ ፕላን ምንጭ፤ ዝግጅት እና አፈጻጸም ጋር የተያያዙ መረጃዎች አያያዝን በተመለከተ .. 24

ክፍል ሦስት .............................................................................................. 26

መደምደሚያ ............................................................................................ 26

ክፍል አራት.............................................................................................. 28

የማሻሻያ ሀሳቦች ........................................................................................ 28

አባሪ 1፡ የኦዲት የትኩረት አቅጣጫና የኦዲት መመዘኛ መስፈርት ........................................... i

አባሪ ሁለት............................................................................................. iii

በሐረር ከተማ በፕላኑ ላይ የተደረጉ ለውጦች ...................................................................iii

በድሬደዋ ከተማ አስተዳደር በፕላኑ ላይ የተደረጉ ለውጦች ..................................................iii

በጅማ ከተማ በፕላኑ ላይ የተደረጉ ለውጦች.................................................................... iv

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. የከተማ ፕላን ማለት አስቀድሞ ለሚወሰን ዘመን የአንድን ከተማ እና አካባቢውን የወደፊት ዕድገት/ልማት በሚፈለገው ዓላማ መሰረት እንዲመራ የሚዘጋጅ ዕቅድ ሲሆን በይዘት ደረጃ የከተማውን መሬት አጠቃቀም፣ የትራንስፖርት ስርዓትን፣ ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ፣ ታሪካዊ፣ የፊዚካላዊና ሌሎች ጉዳዮችን ሊያካትት ይችላል፡፡ የፕላኑ ውጤት (output) የሚገለጸው በካርታና በዝርዝር የፅሑፍ ሰነዶች ነው፡፡
2. ዘመናዊ የከተማ ፕላን ዝግጅት በኢትዮጵያ የተጀመረው ከሰባት አስርት ዓመታት በፊት በጣልያን ወረራ ወቅት ነው፡፡ ፕላኑ አጠቃላይ ንድፍን ብቻ የሚያሳይና ተዘርዝሮ ያልቀረበ ነበር፡፡ ብዙም ሳይቆይ ደገሞ በሁለት የኢጣሊያ የሥነ ሕንፃ ሙያተኞች የተሻለ ፕላን ሊዘጋጅ በቅቷል፡፡ ይሁንና ለአዲስ አበባ በወቅቱ የተዘጋጁት እነዚህ ፕላኖች ነጮች፣ አበሾችና የተለያዩ ጎሳዎች የሚኖሩባቸውንና የሚጠቀሙባቸውን አካባቢዎች በመለየት ላይ ያተኮሩ ነበሩ፡፡ ከነፃነት በኋላም በውጭ ሀገር ባለሙያዎች የከተማ ፕላን የማዘጋጀቱ ስራ የቀጠለበት ሁኔታ ታይቷል፡፡ ሆኖም ግን ለአዲስ አበባ ጭምር ፕላኖቹ በአብዛኛው በአንድ ሲበዛ ደግሞ በሁለት የከተማ ፕላን ሙያተኞች ብቻ መዘጋጀታቸው የሚፈለገውን ውጤት ሊያስገኝ አልቻለም፡፡በተጨማሪም በማህበረ-ኢኮኖሚያዊ መረጃዎች ላይ ያልተመሰረተና ፊዚካል ፕላኖች መሆናቸው ከቶፖግራፊ ካርታዎች ችግርና ከሌሎች ምክንያቶች ጋር ተዳምሮ የአፈፃፀም ደረጃውን በአብዛኛው ዝቅተኛ ሊያደርገው ችሏል፡፡
3. ከ1979 ዓ.ም ጀምሮ የከተማ ፕላን ተቋማዊ ቅርፅ ይዞ በአገር ውስጥ ባለሙያዎች መዘጋጀት መጀመሩ እና የተለያዩ ባለሙያዎችን ግብአት ለማካተት የተደረገውም ጥረት አዎንታዊ እርምጃ ቢሆንም በሽፋንም ሆነ በጥራት ሲታይ የሚፈለገውን ያህል ውጤታማ ነበር ለማለት ግን አይቻልም፡፡የመሠረታዊ ካርታ በተፈለገው ብዛትና ጥራት አለመዘጋጀት፤ የሰለጠነ የሰው ኃይልና በአጠቃላይ የአቅም ውስንነት፣ የመረጃ እጥረትና የመሳሰሉትም ለችግሩ አስተዋጽኦ ያላቸው ምክንያቶች ቢሆኑም በዋነኛነት የተዘጋጁት ፕላኖች በካርታ ዝግጅት (ፊዚካል ፕላን) ላይ ያተኮሩና የነዋሪውን ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ግምት ውስጥ ያስገቡ አልነበሩም።

4. አንዱና ዋናው የከተማ መሬት አጠቃቀም ፕላን ሚና በየጊዜው ቁጥራቸው እየጨመረ የሚመጡ ከተሞችን በፕላን መምራት እንዲሁም በነባር ከተሞች እያደገ የሚመጣውን የከተማ ሕዝብ ብዛት ፍላጎት የሚያስተናግዱ ተጨማሪ ቦታዎችን መያዝ ነው፡፡

5. በዓለም ላይ በርካታ የፕላን አይነቶች ሲኖሩ አሁን በኢትዮጵያ እንዲሰራባቸው የተፈቀዱት ሁለት ዓይነት ፕላኖች ማለትም መዋቅራዊ ፕላን (Structure Plan)፣ የአካባቢ ልማት ፕላንና (Local Development Plan) የሚባሉት ናቸው፡፡ ፕላን ከተዘጋጀ በኋላ በአብዛኛው የመሬት አጠቃቀሙን ለማስፈፀም የየአካባቢው ዝርዝር ፕላኖች የሚያስፈልጉ ሲሆን የማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን ተግባራዊ ለማድረግ ደግሞ የተለያዩ ፕሮጀክቶችንና ፕሮግራሞችን መንደፍ ያስፈልጋል፡፡

6. ፕላን የሚዘጋጅለት ከተማ ከመቆርቆሩ በፊት ጀምሮ የነበሩ ታሪካዊ ክስተቶች፣ ድርጊቶች፣ የሰው ሰራሽም ሆነ ተፈጥሮአዊ ሁኔታዎችና አቀማመጦች፣ የህዝብ አሰፋፈርና የአመሰራረት መልክና (በግብታዊነት ወይም በጥናታዊ ሂደት መሆኑ) ቅደም ተከተላዊ ሂደቶች፣ የማዘጋጃ ቤታዊና የከተማዊ አገልግሎቶች አጀማመርና እድገት መቼ፣ የትና እንዴት እንደሆነ የሚዳሰስበት ነው፡፡ በአጠቃላይም የከተማው ታሪካዊ የእድገት ጉዞ የቅርስና የቱሪዝም መስህብ ገጽታዎችንና የመሳሰሉትን በሚመለከት ጥናታዊ ትንታኔዎች የሚቀርቡበት ነው፡፡

## የከተሞች ፕላን ኢንስቲትዩት አመሰራረት፤

7. በ1979 በአዋጅ ቁጥር 317/79 የብሔራዊ ከተሞች ፕላን እንስቲትዩት እንዲቋቋም ተደርጎ በስሩም አራት የተለያዩ የጂኦግራፊ፤የኢኮኖሚ፤የኢንጅነር፤ የንድፍ የመሳሰሉ ስራዎችን የሚሰሩ አራት መምሪያዎች ነበሩት፡፡በመቀጠልም በአዋጅ ቁጥር 450/1997 የፌዴራል የከተሞች ፕላን ኢንስቲትዩት ተቋቁሞ የሚከተሉትን ዓላማዎችን እንዲሰራ ተሰቶታል፡፡ እነርሱም የከተማ ፕላን ዝግጅት እና አፈጻጸም በሚመለከት ለክልሎች፤ለከተሞች እና ለግሉ ዘርፍ የአቅም ግንባታ እጋዥ ማድረግ ፤የከተማ ፕላንን በሚመለከት የምክር አገልግሎት መስጠት ፤መሠረታዊ የከተማ ነክ መረጃዎችን መሰብሰብና የመረጃ ማዕከል ሆኖ ማገልገል፤ እና ከተሞች በፕላን የሚመሩ ከአካባቢያቸው ገጠር ጋር ጠንካራ ቁርኝት ያላቸውና የፈጣን ልማት ማዕከላት እንዲሆኑና የተመጣጠነ የአከታተም ሥርዓት ለማምጣት የሚያስችል ከተማ ፕላን መዘጋጀት የሚሉ ናቸው፡፡ ኢንስቲትዩቱ ተጠሪነቱ ለፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ሆኖ ቆይቷል፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ አመሰራረት

8. ከ1998 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 471/98 የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ተቋቁሞ የመንግሥት የልማት አቅጣጫን በመከተል የከተማን፤የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪን እና የመንገድ ዘርፍን እንዲመራና እንዲያስተባብር ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡

9. በተጨማሪም በዚሁ አዋጅ የፌዴራል የከተሞች ፕላን ኢንስቲትዩት ተጠሪነቱ ለሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር እንዲሆን ተደርጓል፡፡ በመቀጠልም በ2000 ዓ.ም የፌዴራል የከተሞች ፕላን ኢንስቲትዩትን ማቋቋሚያ አዋጅ ለመሻር አዋጅ ቁጥር 558/2000 ወጥቶ ለኢንስቲትዩቱ ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት ለሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ተላልፈዋል፡፡

10. በተመሳሳይም ወቅት የተመጣጠነና የተቀናጀ ብሔራዊ፤ክልላዊና አካባቢያዊ ዕድገትን ለማምጣት ይቻል ዘንድ ፕላን ሳይኖራቸው ቁጥራቸው እየጨመረ የመጡ ከተሞችን ትክክለኛና ራዕይ ባለው የከተማ ፕላን መምራትና መቆጣጠር በማስፈለጉ፣ የከተማ ፕላን አዋጅ ቁጥር 574/2000 ወጥቷል፡፡

11. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን በወጣው በአዋጅ ቁጥር 691/2003 የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በሚል የተደራጀ ሲሆን ፤በ2005 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 803/2005 በወጣው አዋጅ ስያሜው የከተማ ልማት፤ቤቶች እና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በሚል እንዲሻሻል ተደርጓል፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ራዕይ፣ ዓላማ፣

ራዕይ

12. ለኑሮ ምቹና ተወዳዳሪ የሆኑ ከተሞች እና ዓለም አቀፍ ደረጃን የጠበቀ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ በ2012 ተፈጥሮ ማየት፡፡

ዓላማ

13. የተቋሙን ተገልጋዮችና ባለድርሻ አካላትን በማስተባበርና በማቀናጀት ደረጃውን የጠበቀ አገልግሎት በከተሞች እንዲቀርብ በማድረግ ከተሞች የልማት ማዕከላት እንዲሆኑና ተወዳዳሪ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ በመገንባት ዜጎችን ተጠቃሚ ለማድረግ ነው፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥልጣንና ተግባር

14. በአዋጅ ቁጥር 691/2003 ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት፡-

- አከታተምን በሚመለከት ጥናት ያካሂዳል፣ የከተሞችን ደረጃ መመዘኛ ያወጣል፣
- ከተሞች የአካባቢያቸው የልማት ማዕከል እንዲሆኑ ሁለገብና የተቀናጀ ድጋፍ ይሰጣል፣
- ከተሞች የአገልግሎት አሰጣጣቸውን እንዲያሻሽሉ የአቅም ግንባታ እገዛ ያደርጋል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በከተሞች ልማት መሰረት የማሰልጠኛና የምርምር ማዕከሎችን ያደራጃል፣
- ከክልሎች ጋር በመተባበር የከተሞች ልማት ከገጠር ልማት ጋር በተቀናጀ መንገድ የሚከናወንበትን ሁኔታ በሚመለከት ጥናት ያደርጋል፣ ተግባራዊ እንዲሆን ያግዛል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፣
- ለፌዴራል መንግሥት ተጠሪ የሆኑ የከተማ አስተዳደሮችን የሥራ እንቅስቃሴዎች ይከታተላል፣
- የከተማ ነዋሪው ሕዝብ ከአቅሙ ጋር የተመጣጠኑ መኖሪያ ቤት እንዲሠራ አጠቃላይ አቅጣጫ ለመቀየስ የሚያስችሉ ጥናቶችን ያካሂዳል ለተግባራዊነታቸውም ለከተሞች የአቅም ግንባታ ድጋፍ ይሰጣል፣
- የከተማ ልማት ሥራ ከድህነት ቅነሳ ጋር የተቀናጀ እንዲሆን ጥናቶችን ያካሂዳል፣ ለተግባራዊነታቸውም ድጋፍ ይሰጣል፣
- የጥቃቅንና የአነስተኛ ተቋማት ልማት እንዲስፋፉ ያደርጋል፣
- ለሌሎች አካላት በሕግ የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የኮንስትራክሽን ሥራ ደረጃዎች ያወጣል፤ መከበራቸውን ይከታተላል፡፡
- ዓለም አቀፍ የተወዳዳሪነት ብቃት ያለው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ለመገንባት የሚያስችሉ የተመቻቹ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ያደርጋል፣
- በፌዴራል መንግሥት በጀት ለሚሰሩ ሕንፃዎች ዲዛይኖችና የግንባታ ውሎች እንዲዘጋጁ በማድረግና የግንባታ ሥራዎችን በመቆጣጠር ረገድ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፣
- መሐንዲሶችና አርክቴክቶችን ይመዘግባል፣ የሙያ ችሎታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ የሥራ ተቋራጮችንና የአማካሪዎችን ደረጃ ይወስናል፣ ከአንድ በላይ በሆኑ ክልሎች ውስጥ መሥራት የሚችሉ ሥራ ተቋራጮችና አማካሪዎች የሥራ ተቋራጮችና የአማካሪዎች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣

- በአገር ውስጥ የሚመረቱ የኮንስትራክሽን እቃዎችን ዓይነትና ጥራት ለማሻሻል የሚረዳ ምርምር ያካሂዳል፣
- ለሌላ የመንግሥት አካል በህግ የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ በፌዴራል መንግሥት ባለቤትነት ሥር የሚገኙ ቤቶች አስተዳደር በአግባቡ እንዲከናወን መደረጉን ያረጋግጣል፣

15. በከተሞች ፕላን አዋጅ ቁጥር 574/2000 መሠረት ለሚኒስቴሩ መ/ቤቱ የተሰጡት ሥልጣንና ተግባር

- ከሚመለከታቸው የፌዴራል መንግሥት አካላት ጋር በመተባበር ብሔራዊ የከተማ ልማት እቅድ ያዘጋጃል፡
- የከተማ ፕላኖች ከዚህ አዋጅ ጋር የሚጣጣሙ ስለመሆናቸው ቁጥጥርና ክትትል በማድረግ በአገሪቱ ውስጥ የተመጣጠነና የተቀናጀ የከተማ ልማት መኖሩን ያረጋግጣል፤
- ለክልል ከተሞችና ለፌዴራል መንግሥት ተጠሪ ለሆኑ ከተሞች የከተማ ፕላንን የልማት በሚመለከት የቴክኒክና የአቅም ግንባታ ድጋፍ ያደርጋል፤
- አፈ-ቃቀድ ደንቦችን አጠቃላይ ተፈፃሚነት በብሔራዊ ደረጃ ይከታተላል፤ይገመግማል፤
- የከተማ ፕላንን የሚመለከቱ መረጃዎችን ያሰባስባል፤ያደራጃል፤ፍላጎቱ ያላቸው ወገኖች እንዲያገኟቸው ያደረጋል፤
- ለአማካሪዎች ፈቃድና ደረጃ ለመስጠት የሚረዱ መመዘኛዎችን ያዘጋጃል፤በከተማ ፕላን አዘገጀጃት ሥራ ለሚሰማሩና በደረጃ እንድ ላይ ለሚመደቡ አማካሪዎች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል፤

ድርጅታዊ መዋቅር

16. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተጠሪነቱ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ሆኖ በአንድ ሚኒስትርና በሁለት ሚኒስትር ዴኤታዎች (ኮንስትራክሽን ዘርፍ ሚኒስቴር ዴኤታ እና የከተማ ልማት ዘርፍ ሚኒስቴር ዴኤታ) ተዋቅሯል፡፡ ተጠሪነታቸው ለሚኒስትሩ የሆኑ ሁለቱን ሚኒስትር ዴኤታዎች ጨምሮ ስድስት ቢሮዎች፤ሁለት ጽ/ቤቶች እና አንድ መምሪያ ሲኖር ፤ ተጠሪነታቸው ለኮንስትራክሽን ዘርፍ ሚኒስቴር ዴኤታ የሆኑ ሁለት ቢሮዎች እና እንድ ድርጅት ሲኖር ተጠሪነታቸው ለከተማ ልማት ዘርፍ ሚኒስቴር ዴኤታ የሆኑ

ሶስት ኤጀንሲዎች፤ሶስት ቢሮዎች እና አንድ ፕሮጀክት ጽ/ቤት እንዳሉት ለመረዳት ተችሏል፡፡ (በአባሪ 1 ተያይዟል፡፡)

የሰው ኃይል፤

17. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለእነዚህ የተለያዩ የሥራ ክፍሎች በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት (BPR) መሠረት የሚያስፈልገው የሰው ሀይል ብዛት 694 ሲሆን በመጋቢት /2006 በሥራ ላይ ያለ 349 ወንድ እና 145 ሴት በድምሩ 494 ሰራተኞች ነበሩት ፡፡ ይህም በትምህርት ደረጃ ሲተነተን 2ኛ ድግሪ 136፤ የመጀመሪ ድግሪ 195፤ ዲፕሎማ 101፤ ሰርተፍኬት 62 መሆኑ ከተከለሰ መረጃ ለመረዳት ተችሏል፡፡

## የፋይናንስ ምንጭ፤

18. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣትና በዕቅድ የያዛቸውን ሥራዎች ለማስፈጸም የሚያስፈልገውን ከመንግሥት በየዓመቱ ከሚመደብ በጀት፣ እንደዚሁም ከእርዳታና ብድር የሚያገኝ ሲሆን ዝርዝሩ በሚከተለው ሰንጠረዥ ላይ ተመልክቷል፡፡

| ዓ.ም | የተመደበ በጀት | | ጠቅላላ የተመደበ በጀት | ጥቅም ላይ የዋለ | | ጥቅም ላይ የዋለ ጠቅላላ ወጪ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | መደበኛ | ካፒታል | | መደበኛ | ካፒታል | በብር | በፐርሰንት |
| 2004 | 50,445,471.00 | 336,680,735.00 | 387,126,206.00 | 38,657,370.00 | 238,630,790.00 | 277,288,160.00 | 71.63% |
| 2005 | 59,423,994.00 | 414,955,532.57 | 474,379,526.57 | 55,065,196.46 | 256,405,715.31 | 311,470,911.77 | 65.66% |
| 2006 | 81,366942.00 | 693,988,070.00 | 775,355,012.00 | 62,52,8687.10 | 386,615,978.43 | 449,144,665.53 | 57.92% |
| 2007 | 100,490,820.00 | 863,701,680.00 | 964,192,500.00 | እስከ 30/01/07 14,009,832.12 | እስከ 30/01/07 118,304,601.51 | እስከ 30/01/07 132,314,433.63 | 13.72% |

## የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ

19. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ የከተማ ፕላን ምንጭ፤ ዝግጅትና እና አፈጻጸም ኢኮኖሚያዊ ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን በማረጋገጥ በሥራው ዙሪያ የሚታዩ የአሠራር ችግሮች ወይም ክፍተቶች ካሉ ችግሮቹን እና መንስኤያቸውን በመለየት ችግሮቹን ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሀሳቦችን ለማቅረብ ነው፡፡

## የኦዲቱ አካባቢ

20. ለኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ

"የከተማ ፕላን ምንጭ፤ ዝግጅትና እና አፈጻጸም፣ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና እና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ"

የሚል ነው፡፡

## የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫ (audit issue) እና የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria)፤

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫ

21. ካላይ በተለየው የኦዲት ካባቢ (audit area) ስር አራት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች እና ሁለት ንዑስ የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ተለይተዋል፡፡ እነሱም፡-

1. የከተማ ፕላን ምንጭ እና ዝግጅት ቀልጣፋና እና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ፤
   - 1.1 የከተማ ፕላንን በሚመለከት የሚደረገው የቴክኒክ እና የአቅም ግንባታ ድጋፍ ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና እና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ፤
   - 1.2 ከተማን መልሶ የማልማት፤ እድሳትን ማከናወንና መምራት በአካባቢ ማእቀፍ ላይ ተመስርቶ በበቂ ምክንያት የተደገፈና የታቀደ መሆኑን ማረጋገጥ
   - 1.3 የከተማ ፕላን ዝግጅትና አፈጻጸም የቴክኒክና አቅም ግንባታ አፈጻጸም ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ
2. የከተሞች ፕላን አፈጻጸም የቁጥጥር፣ክትትልና ግምገማ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ፤
3. የከተማ ፕላን አፈጻጸምን በተመለከተ ቅንጅታዊ አሰራር እና የመረጃ ልውወጥ ተግባር ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና እና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ፤የሚሉት

ናቸው፡፡

የኦዲት መመዘኛ መስፈርት፣

22. ከላይ ለተመረጡት አራት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issue) እና ሁለት ንዑስ የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ለመገምገም የሚያስችል 42 የኦዲት መመዘኛ

መስፈርቶች (Evaluative Criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ (የኦዲት መመዘኛ መስፈርቱ በአባሪ 1 ተያይዟል፡፡)

## የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ


23. ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (Ethiopian Performance Audit Standards) እና ለመ/ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 669/2002 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ነው፡፡ ዝርዝር ኦዲቱ የሸፈነው ከ2004-2006 ያሉትን የሶስት በጀት ዓመታት እና የ2007 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የሥራ ክንውኖችን ነው፡፡ ኦዲቱ በዋነኛነት የተከናወነው በከተማ ልማት፤ቤቶች ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ሲሆን የኦዲት ቡድኑ የሚኒስቴር መ/ቤቱን አሠራር የሚመለከቱ የተለያዩ አዋጆች፣ ሠነዶችና ማስረጃዎችን (የተለያዩ የመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ የጥናት ሪፖርቶች፣ የየአመቱን ዕቅድና የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት፣ የስትራቴጅክ ዕቅድ) የሥራ አመራር (የማናጅመንት) ስብሰባ ቃለጉባኤ፤የከተማ ፕላን አፈጻጸም ገምገማ ግብረ-መልስ ሪፖርት፤የውስጥና የውጭ ኦዲት ሪፖርቶች የተለያዩ መመሪያዎችን እና ጥናቶችን የከለሰ ሲሆን ጉዳዩ የሚመለከታቸውን የሚኒስቴር መ/ቤቱን የሥራ ኃላፊዎችን፣ የከተማ ፕላን አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ግብረመልስ መምሪያ ኃላፊ፤የከተማ ፕላን ጽዳትናውበት ስልጠና መምሪያ ከፍተኛ ኤክስፐርት፤የከተማ ፕላን ጽዳትና ውበት ጥናት ምርምር መምሪያ ኃላፊ፤የአዲስ አበባ ማስተር ፕላን የግምገማ ቡድን አባልን አነጋግሯል፡፡

24. በተጨማሪም በናሙና የመስክ ጉብኝት በተደረገባቸው በጅማ ከንቲባ ጽ/ቤት፤ በጅማ ከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ኤጀንሲ፤በጅማ ከተማ ማዘጋጃ ቤት፤በጅማ ከተማ አካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት፤በድሬደዋ ከተማ አስተዳደር የከተማ ፕላንና መረጃ ዝግጅት ቢሮ፤ በድሬደዋ ከተማ ጂኦግራፊር (ሪጂናልፕላነር) ቢሮ፤በድሬደዋ ከተማ የህብረተሰብ ተሳተፎ ልማት ኤጀንሲ በድሬደዋ ከተማ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ፤በሐረሪ ክልል አስተዳደር የከተማ ፕላና መረጃ ኃላፊ ቢሮ ፤በሐረሪ ክልል የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን፤በኦሮሚያ የከተሞች ፕላንናኢንስቲትዩት፤በአዲስ አበባ የከተማ ፕላን ኢንስቲትዩት በመገኘት የከተማ ፕላንን በሚመለከት መረጃዎችን በመከለስና ቃለመጠይቅ በማቅረብ እና ለደቡብ ብሔር በሔረሰቦች ክልላዊ መንግሥት ለንግድ ኢንዱስትሪና ከተማ ፕላን ቢሮ ጥያቄ በመላክ ነው፡፡


25. በተጨማሪም የኦሮሚያ ከተማ ልማት ዳይሬክተር እንደዚሁ ለኦዲቱ መረጃ ለመስጠትም ሆነ ቃለ መጠይቅ ለመመለስ በተደጋጋሚ ተጠይቀው ፈቃደኛ ሆነው አልተገኙም፡፡

## የሥራ ሂደት መግለጫ   (process description)

### በከተማ ፕላን የሬጉላተሪና ድጋፍ አሰጣጥ ረገድ የጥናትና ምርምር የስራ ፍሰት




# በከተማ ፕላን የሬጉላተሪና ድጋፍ አሰጣጥ ረገድ የስልጠና የስራ ፍሰት




3

# በከተማ ፕላን የሬጉላተሪና ድጋፍ አሰጣጥ ረገድ የክትትልና ግምገም የስራ ፍሰት



# ክፍል ሁለት

## ግኝቶች

### 2.1 የከተሞችን ፕላን ምንጭ እና ዝግጅት ቀልጣፋና እና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ፤

**ብሔራዊ የከተማ ልማት አቅድ (National Urban development scheme) መዘጋጀቱን በተመለከተ**

26. በአዋጅ ቁጥር 574/2000 መሰረት ሚኒስቴር መ/ቤቱ ብሔራዊ የከተማ ልማት ዕቅድ (National Urban development scheme) ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡ ፕላኑ በሚዘጋጅበት ጊዜም አገር አቀፍ የልማት ስትራቴጂና ዕቅድ ላይ ሊመሰረትና የሚመለከታቸውን የፌዴራል እና የክልል አካላትን ሊያሳትፍ ይገባል፡፡

27. ይሁን እንጂ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ብሔራዊ የከተማ ልማት ዕቅድ አለመዘጋጀቱ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡ ነገር ግን የከተሞች ልማትና ህዝብ አሰፋፈር ፕላን (National Urban Development Spatial plan)ጥናት የብሄራዊ የከተማ ልማት ዕቅድ (National developmen Scheme) አግባብ ያላቸውን ባለድርሻ አካላትን ባሳተፈ መልኩ ከታኅሣሥ 2006 ጀምሮ በውጭ አማካሪ ድርጅት አማካይነት ዝግጅቱ ሲካሄድ የቆየና በታኅሣሥ ወር 2007 አጠናቆ ጥናቱን ማቅረቡ ታውቋል፡፡

28. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው ብሔራዊ የከተማ ልማት ዕቅድ (National Urban development scheme) ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሲሆን ጥናቱ በሁለት ሰነዶች የቀረበ ሆኖ አንደኛው የነባራዊ ሁኔታ እና የችግሮች ዳሰሳ የሚያሳይ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በዚህ ዳሰሳ ላይ በመመስረት የተዘጋጀው አማራጭ የኢትዮጵያን የወደፊት ከተማነት የሚያሳይ ሰነድ ነው ብለዋል፡፡ በዚሁ ጥናት ላይ ተመስርቶ አማራጭ የፖሊሲ ሃሳብ የያዘ ረቂቅ መዘጋጀቱን ገልጸዋል፡፡

29. በዚህ መልክ የተወሰዱ እርምጃዎች መልካም ጅማሬዎች ቢሆኑም የቅድመ ፕላን ሥራዎች ተጠናቅቀው ብሔራዊ የከተማ ልማት አቅድ ባለመዘጋጀቱ እርሱን መሰረት ተደርገው መዘጋጀት የነበረባቸው ክልላዊ የከተማ ልማት ዕቅድ ፕላን እንዳይዘጋጅ እንቅፋት ከመሆኑም በላይ ፤ በአገሪቱ ውስጥ የተመጣጠነና የተቀናጀ ብሔራዊ፤ ክልላዊና አካባቢያዊ ዕድገትን ለማምጣት የሚያስችል የከተማ ልማት እንዳይኖርና

የአገሪቷ የወደፊት የከተሞች ዕድገት/ልማት በሚፈለገው መሰረት እንዳይመራ መንስዔ ሊሆን ይችላል፡፡

### ክልላዊ የከተማ ዕቅድ/ፕላን መዘጋጀቱን በተመለከተ

30. በአገር አቀፍ ደረጃ የተዘጋጀውን ብሔራዊ የከተማ ልማት ዕቅድ መሰረት ያደረገ ክልላዊ የከተማ ልማት ዕቅድ/ ፕላን (Regional urban development Plan) ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ እርሱንም መሰረት በማድረግ ለእያንዳንዱ ከተማ የከተማ ልማት ፕላንና (Local Development Plan) የአካባቢ ልማት ፕላን ሊዘጋጅ ይገባል፡፡
31. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት በኦሮሚያና በሐረሪ ክልሎች፣ በአዲስ አበባ እና በድሬደዋ ከተማ መስተዳድሮች ክልላዊ የከተማ ልማት ዕቅድ ፕላን አለመዘጋጀቱ ታውቋል፡፡ የአካባቢ ልማት ፕላንን ለማዘጋጀት ክልላዊ የከተማልማት ዕቅድ ፕላን ያልተዘጋጀ በመሆኑ፣ የሀረሪ ከተማ የአካባቢ ልማት ፕላን ከዚህ በፊት የተዘጋጁ የሌሎች ከተሞች ማስተር ፕላንን በመጠቀም የተዘጋጀ ሲሆን፣ የጅማ ከተማም እንደዚሁ በሌሎች ከተሞች ተሞክሮ ላይ በመመርኮዝ የአካባቢ ልማት ፕላንን አዘጋጅተዋል፡፡ የድሬደዋ ከተማ በ5 ዓመት እንደገና መሰራት ሲገባው ባልተሰራ የተቀናጀ የልማት ፕላን( Inetegrated devolopmenet plan) ፕላንን በመጠቀም የአካባቢ ልማት ፕላን እንዳዘጋጁ ታውቋል፡፡
32. በመጀመሪያ ብሔራዊ ቀጥሎም ክልላዊ የከተማ ፕላን ባለመሰራቱ ምክንያት ከተሞች ከከተሞች እንዲሁም ከተሞች ከገጠሮች ጋር የሚኖራቸው ትስስር ወጥ በሆነ መልኩ እንዳይተገበር ችግር ይፈጥራል፡፡

### በከተማ ፕላን ዝግጅት ወቅት የሚመለከታቸው አካላት ተሳትፎን በተመለከተ

33. የከተሞች ፕላን በሚመነጭበትና በሚዘጋጅበት ወቅት የሕዝብ ተሳትፎ፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት እንዲኖር በማድረግ የህብረተሰቡ ፍላጎት መሟላቱ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡
34. የከተሞች ፕላን በሚመነጭበትና በሚዘጋጅበት ወቅት የመሰረተ ልማት አቅራቢዎችና የሕዝብ ተሳትፎን በማካተት ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ ግልጽነትና ተጠያቂነት እንዲኖር በማድረግ የህብረተሰቡ ፍላጎት መሟላቱን ለማረጋገጥ የተዘጋጀው የከተሞች ፕላን ከመጽደቁ በፊት የከተማው ህዝብ እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት እንዲወያዩበት ሊደረግ ይገባል፡፡

35. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት ከተሞች ከህዝብ ተወካዮች ጋር ውይይት የሚደረግ ሲሆን፤የመሰረተ ልማት አቅራቢ ከሆኑት ጋር በቅርበት ለመስራት የሚያስችል ስርዓት ያልተዘረጋ በመሆኑ፣ በፕላን ዝግጅት ወቅት የመሰረተ ልማት ተቋማት ፍላጎትና ስታንዳርድን በማምጣት ለማካተት ጥረት ቢደረግም የተዘረጋ የአሰራር ስርአት ባለመኖሩ የተነሳ ተቀናጅቶ በጋራ ባለመንቀሳቀስ በሚፈጠር ክፍተት ምክንያት መንገዶች መበላሸታቸውን፣ የውሃ ማፍሰሻ ቱቦዎች የቁሻሻ መጣያ እየሆኑ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለጅማ ለድሬደዋና ለሀረሪ፤ለኃላፊዎች ከቀረበው መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡

36. ከዚህ በተጨማሪ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት ክልሎች ውስጥ በሀረሪ ክልልና በድሬደዋ ከተማ የጸደቀው የከተማ ፕላን ለትግበራ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት እንዲመሩበት (እንዲመክሩበት) ማስገንዘቢያ የማይሰጥ በመሆኑ፡ በዚህም ምክንያት ባለድርሻ አካላት የመሰረተ ልማት አቅራቢ የሆኑት ባለድርሻ አካላት የመንገዶች ባለስልጣን፣ ውሃና ፍሳሽ፣ ፅዳትና ውበት፣ አካባቢ ልማት፣ መብራት ኃይል፣ ቴሌኮሙንኬሽን እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የተቀናጀና የተናበበ ዕቅድ እንዳያቅዱ እንቅፋት እንደሆነ ለድሬደዋ ከተማ ኃላፊዎች ከቀረበው መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡

37. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች የተጠቀሱት ችግሮች መኖራቸው እሙን መሆኑን እና በመጋቢት 2006 በተዘጋጀው የከተሞች ፕላንና ስትራቴጂ ሰነድ ውስጥ እንደ አንድ የትኩረት አቅጣጫ መወሰዱን ለነባራዊ ሁኔታ በሰጡት አስተያየት ገልጸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ይህን በተመለከተ ረቂቅ አዋጅ እየተዘጋጀ ሲሆን ህዝብ እንዴት መሳተፍ እንዳለበት የሚገልጽ ማንዋልም ተዘጋጅቷል፡፡

38. በፕላን ዝግጅት ወቅት ተመካክሮ ለመስራት የሚያስችል የተዘረጋ ስርዓት ባለመኖሩ የተናበበ እቅድ ለማቀድም ሆነ ለማስፈጸም አስቸጋሪ ከመሆኑም በላይ ባለድርሻ አካላትም እቅዳቸውን በተናጠል ማቀዳቸው የመሰረተ ልማት ዝርጋታው አንዱ የሠራውን ሌላው እያበላሸ የሀብት ብክነት ሊያስከትል ከመቻሉም በላይ ህብረተሰቡ በፕላን ዝግጅት በተገቢው እንዲሳተፍ ባለመደረጉ የፕላን ጥሰት እንዳይከሰት በመከላከል ረገድ ህብረተሰቡና ሌሎች ባላድርሻ አካላት ድርሻውን እንዳይወጣ ያደርጋል፡፡

## ከተማን ለማደስ ምቹ የመኖሪያና የሥራ አካባቢ ለመፍጠር የሚያስችል እቅድ ስለመዘጋጀቱ፤

39. የከተሞች ፕላን ሲዘጋጅ ምቹ የመኖሪያና የሥራ አካባቢ ለመፍጠር የአረንጓዴ አካባቢ ስፍራ እና የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች በግልጽ ተለይተው ሊቀመጡና በፕላኑ መሰረት ሊተገበሩ ይገባል፡፡ የከተሞች መልሶ ማልማት ዕቅድም ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

40. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ባየናቸው በጅማ ፣በድሬደዋ፤ በሀረሪ እና በአዲስ አበባ ከተሞች ከተማን የማደስ ተግባር፤ በአንድ ከተማ ውስጥ የሚታዩትን የፈራረሱ፤ ያረጁ፤ የተተዉ መዋቅሮች በከፊል ወይም በሙሉ በማስወገድ ምቹ የመኖሪያና የሥራ አካባቢ ለመፍጠር የሚያስችል እቅድ እንዲዘጋጅ አልተደረገም፡፡

41. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ካየናቸው ከተሞች የጅማና የድሬዳዋ ከተሞች የአካባቢ ልማት ፕላን ሲዘጋጅ የአረንገዴ አካባቢ ስፍራ እና የመኪና ማቆሚያ ቦታ እንዲካተት ቢደረግም ተግባራዊ አለመደረጉ ታውቋል፡፡ በአንዳንድ ቦታ ለአረንጓዴ ቦታ በተከለለ መሬት ላይ ከ60-70 የሚሆን አባወራ የሰፈረበትና በተጨማሪም የስፖርት ማዘውተሪያም ሆኖ እንደሚያገለግል ለኃላፊዎች ከቀረበው መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

42. ስለጉዳዩ የከተሞቹ የሚመለከታቸው ኃላፊዎች ተጠይቀው የጅማ ከተማ በፕላኑ ላይ ቢካተተም ቀደም ሲል በስፍራው የሰፈሩ ሰዎችን ለማንሳት የካሳ ክፍያ መክፈል ስላልተቻለ ወደ ተግባር አልመገባቱን ገልጸዋል፡፡ በድሬደዋ ከተማ ፕላኑ ላይ እንዲካተት ቢደረግም ተግባራዊ አለመደረጉን፣ በአፈጻጸም ደረጃ መልሶ የማልማት ስራ በተወሰነ ደረጃ የተጀመረ ቢሆንም ይህንንም በካቢኔ በማፀደቅ እንጂ ለምክር ቤት ቀርቦ እንዲጸድቅ ተደርጎ ተግባራዊ አለመደረጉን ገልጸዋል፡፡

43. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ በሰጡት አስተያየት የመሬት አጠቃቀም ድልድል የሚደረግ ቢሆንም በፕላን ትግበራ ወቅት ግን ጥሰት እንደሚፈጸም ገልጸዋል፡፡ በሀገራችን ከ20,000 የህዝብ ቁጥር በላይ ላላቸው ከተሞች እንዲዘጋጅ ሲመረጥ ውጤታማ የመሬት አጠቃቀምን በማረጋገጥበና ወቅታዊና ተለዋዋጭ ሁኔታን በማገናዘብ የከተሞችን እድገትበአስተማማኝ ሁኔታ ይመራል ተብሎ የታመነበት በመሆኑለዚሁ ማስፈጸሚያ የሚሆን የመዋቅራዊ ፕላን ማዘጋጃና መተግበሪያ ማንዋል ለሁሉም ክልሎች መጋቢት 2006 ማሰራጨታቸውን ገልጸዋል፡፡

44. በፕላን ላይ የተካተቱት የአረንጓዴ ሥፍራዎችም ሆነ የመኪና መቆሚያ ቦታዎች ወደ ተግባር አለመለወጥ ከተሞች ለነዋሪዎቻቸው ምቹ የመኖሪያና የሥራ አካበቢ ለመፍጠር የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ይፈጥራል፡፡

## የአካባቢ ልማት ፕላን በሚመለከተው አካል ጸድቆ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ

45. የከተሞች የአካባቢ ልማት የመጨረሻ ረቂቅ ፕላኖች በየከተሞቹ ምክር ቤቶች ውይይት ከተደረገባቸው በኋላ በሚመለከተው አካል እንዲጸድቁ እና ለሚመለከታቸው የክልል ወይም የፌዴራል አካላት በወቅቱ እንዲደርሱ ሊደረግ ይገባል፡፡ ለውጥ የተደረገባቸው ቦታዎች በአካባቢ የልማት ፕላን (Local Development Plan) ላይ እንዲሰፍሩና በሚመለከተው አካል እንዲጸድቁ ሊደረግ ይገባል፡፡

46. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በድሬደዋ ከተማ ምክር ቤቱ የተቋቋመው በ2000 ዓ.ም ሲሆን የድሬደዋ የተቀናጀ ልማት ፕላን (Integrated Development Plan) የተሰራው በ1997 ዓ.ም. የነበረ ቢሆንም እስካሁን ያልተከለሰና ለከተማው ምክር ቤት ቀርቦ አለመጽደቁ፣ የአካባቢ ልማት ፕላን (Local Development Plan) በከተማው ካቢኔ ቢጸድቅም ለከተማው ምክርቤት ቅርቦ አለመጽደቁ ታውቋል፡፡ በከተማው እየተሰራ ያለው የድሬደዋ ሪፈራል ሆስፒታል በአካባቢ ልማት ፕላን ላይ ያልሰፈረና በካቢኔም ሆነ በምክር ቤት እንዲጸድቅ ያልተደረገ ነው፡፡ በሀረሪ ክልል በየጊዜው የአካባቢ ልማት ፕላን ለውጦች ተደርገው ለካቢኔ ቀርበው ሳይጸድቁ ወደ ትግበራ የተገባ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

47. ስለጉዳዩ የከተሞቹ ኃላፊዎች ተጠይቀው በቀረበላቸው መጠይቅ ሲመልሱ በድሬዳዋ የአካባቢ ልማት ፕላን (Local Development Plan) በከተማው ካቢኔ ቢጸድቅም በመጀመሪያ መጽደቅ የነበረበት መዋቅራዊ ፕላኑ (Structural Plan) ለምክር ቤት ቀርቦ ስላልፀደቀ የአካባቢ ልማት ፕላን እንዲጸድቅ ለምክር ቤቱ አለመቅረቡን ገልጸዋል፡፡በሀረሪ የተደረጉ ለውጦችን በማሰባሰብ ለካቢኔ አቅርቦ ለማፅደቅ በዝግጅት ላይ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

48. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ በሰጡት አስተያየት በከተማ ፕላን አዋጅ አንቀጽ 16 መሰረት ማጽደቅና መፈራረም ይጠይቃል፡፡ ስለሆነም ይህ ካልሆነ መታረም አለበት ብለዋል፡፡

49. የሚሰሩት የአካባቢ ልማት ፕላኖች በሚመለከታቸው አካላት ቀርበው አለመጽደቃቸው አስፈጻሚዎች በአንድ ከተማ ውስጥ የሚሰሩ ሥራዎች ያልተናበቡ እንዲሆኑ፣

በሚተገበሩበት ጊዜ አንዱ ሲገነባ ሌላው እንዲያፈርስ ምክንያት ከመሆኑም በላይ የከተሞቹን እድገት ወደ ኋላ እንዲጓተትና ለሀብት ብክነት ሊዳርግ ይችላል፡፡

## 2.2 የከተማ ፕላንን በሚመለከት የሚደረገው የቴክኒክ እና የአቅም ግንባታ ድጋፍ ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና እና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ፤

### የቴክኒክና የአቅም ግንባታ ድጋፍ የአሰራር ማንዋል ዝግጅትን በተመለከተ

50. ፕላንን በሚመለከት ለሚደረግ የቴክኒክና የአቅም ግንባታ ድጋፍ የአሰራር ማንዋል በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ ሲዘጋጅም የሚመለከታቸው አካላትን ሊያሳትፍና አስተያየት እንዲሰጡበት ሊደረግ ይገባል፡፡

51. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት እንደተቻለው የፕላን ዝግጅትን በሚመለከት መመሪያ፣ስታንዳርድና ፕሮግራሞችን ለማዘጋጀት ቀደም ብሎ ያለውን ክፍተት ለማወቅ እንዲቻል የዳሰሳ ጥናት በማድረግ ጥናቱን መነሻ በማድረግ ማንዋሉም ሆነ ደረጃዎችን እና ፕሮግራሞች እንዳልተዘጋጁ ታውቋል፡፡

52. በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት እንደተቻለው ለክልል ከተሞችና ለፌዴራል መንግሥት ተጠሪ ለሆኑ ከተሞች የከተማ ፕላንን በሚመለከት የቴክኒክና የአቅም ግንባታ ድጋፍን የሚመለከት የአሰራር ማንዋል እንዲዘጋጅ አልተደረገም፡፡

53. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት የድሬደዋ ከተማ መስተዳድርና የሀረሪ ክልል ኃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በአገር አቀፍ ደረጃ የፕላን አዘገጃጀትና አፈጻጸም ማንዋል በሚኒስቴር መ/ቤቱ ተዘጋጅቶ አስተያየት እንዲሰጡበት ተልኮላቸው አስተያየታቸውን ሰጥተው የተመለሰ ቢሆንም እስካሁን በሚመለከተው አካል ጸድቆ ሥራ ላይ እንዲውል አለመደረጉን ገልጸዋል፡፡

54. ለአዲስ አበባ ከተማ ፕላን ኢንስቲተዩት የቢሮ ኃላፊም ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ስታንዳርዶችን ማንዋሎችን በማዘጋጀት ስልጠና ለመስጠት ጥረት እያደረገ ቢሆንም ነገር ግን የአዲስ አበባ ከተማ ውስብስብና ዓለም አቀፍ ከተማ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ዓለም አቀፍ ተሞክሮና ድጋፍ የሚገኝበት ሁኔታ አልተመቻቸም ብለዋል፡፡

55. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ በሰጡት አስተያየት የቴክኒክና የአቅም ግንባታ ድጋፍ እየተደረገ የሚገኝ ሲሆን የአሰራር ማንዋል በቀጣይ እንደሚዘጋጅ በመጋቢት 2006 የከተማ ፕላን ዝግጅትና ትግበራ ስትራቴጂ መዘጋጀቱን ገልጸዋል፡፡

56. የፕላን አፈጻጸም ማንዋል (መመሪያ) ተዘጋጅቶ ተግባራዊ አለመደረጉ በሁሉም ከተሞች ወጥ የሆነ የፕላን ዝግጅት እንዳይኖር ከማድረጉም በላይ የየከተሞቹን ክፍተት በመለየት ተገቢውን ቴክኒካዊም ሆነ ቁሳዊ ድጋፍ መስጠትን አዳጋች ያደርገዋል፡፡

## የጥናት ሰነዶች በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን በተመለከተ

57. ለከተማ ፕላን ዝግጅትና አፈጻጸም ጥናቶች ሊጠኑ ይገባል፡፡ የተዘጋጁ የጥናት ሰነዶች ተግባራዊ እንዲደረጉ ለሚመለከታቸው አስፈጻሚ አካላት ሊደርሳቸው ይገባል፡፡ ጥናቶቹም በትክክል ሥራ ላይ የዋሉ ለመሆኑ ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

58. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት እንደተቻለው የከተማ ፕላን ዝግጅትና አፈጻጸምን በተመለከተ የተለያዩ የጥናት ሰነዶች በሚኒስትር መ/ቤቱ የተዘጋጁ ቢሆንም የጥናት ሰነዶቹ በናሙና በታዩት ለሀረሪ ክልልና ለድሬደዋ ከተማ የደረሱ ሲሆን ለአዲስ አበባና ለጅማ ከተማ እንዳልደረሳቸው ገልጸዋል፡፡ የጥናት ሰነዶቹ በደረሳቸው በድሬደዋ ከተማ መስተዳድርና በሀረሪ ክልል በትክክል ሥራ ላይ እንዲውሉ አልተደረገም፡፡ ይህንንም በሚመለከት በሚኒሰቴር መ/ቤቱ ክትትልና ቁጥጥር ተደርጎ የማያውቅ መሆኑን ለኃላፊዎች ከቀረበው መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ በሰጡት አስተያየት ሰነዶቹ ሥራ ላይ ስለመዋላቸው በተመረጡት የናሙና ከተሞች በፌዴራል ደረጃ እና በክልል ደረጃ ክትትል በማድረግ በአካልና በጽሁፍ ግብረመልስ ተሰጥቷል ቢሉም እስካሁን በኦዲቱ ለማረጋገጥ እንደተቻለው በሚኒስቴር መ/ቤቱ ክትትልና ቁጥጥር የሚደረገው በፕላን ዝግጅት እና ትግበራ ላይ ብቻ በመሆኑ የተሰጠውን መልስ እንዳለ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

59. ለከተማ ፕላን ዝግጅትም ሆነ አፈጻጸም የሚረዱ የጥናት ሰነዶችን ተዘጋጅተው ለሚመለከታቸው አስፈጻሚ አካላት ደርሶ ተግባራዊ አለመደረጉ ለጥናቶቹ የሚወጣው ሀብት የባከነ እንዲሆን ከማድረጉም በላይ የጥናቱ ውጤት ቢተገበር ኖሮ ይገኝ የነበረውን ጠቀሜታ ያሳጣል፡፡

## 2.3 የከተሞች ፕላን አፈጻጸም የቁጥጥር፣ክትትልና ግምገማ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤

### ማንኛውም የጸደቀ ፕላን በሚተገበርበት ወቅት የፕላን ጥሰት እንዳይኖር ክትትልና ቁጥጥር መደረጉን በተመለከተ

60. የከተማ ፕላን በሚተገበርበት ወቅት የፕላን ጥሰት እንዳይኖር ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡ በፕላኑ ላይ ከተመለከተው ውጭ ለሚፈጸም ጥሰት በወቅቱ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ የልማት አፈ.ቃቀድ ደንቦችን አጠቃላይ ተፈጻሚነት በሀገር አቀፍ ደረጃ ክትትልና ግምገማ ሊደረግ ይገባል፡፡ የከተማ ፕላን በጊዜው የሚመጣውን ተለዋዋጭ የከተማ ዕድገት ባህሪ ያገናዘበ ሊሆን ይገባል፡፡

61. ፕላን በሚዘጋጅበትና በሚተገበርበት ወቅት የፕላን ጥሰት እንዳይኖር በናሙና የታዩት የድሬዳዋ፣ የሐረር፣ የመቀሌ፣ የአዳማ፣ የደሴ፣ እና የጅማ ከተሞች ፕላን ዝግጅትና ትግባራ ላይ ላይ የክትትልና የቁጥጥር ሥራ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተሰራ ሲሆን፤ በባህር ዳር፣ በሀዋሳ እና በአዲስ አበባ ከተሞች ፕላን ዝግጅትና ትግበራ ላይ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ክትትልና ቁጥጥር ስለመደረጉ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ በሚኒስቴር መ/ቤቱ መረጃ አልቀረበም፡፡ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ በሰጡት አስተያየት በሀገሪቱ ባሉ ከተሞች የፕላን ጥሰትን ለመቆጣጠር ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ሲሆን ባለው የአቅም ውስንነት ምክንያት በባህር ዳር በሀዋሳ እና በአዲስ አበባ የክትትልና ቁጥጥር ሥራ ለማከናወን በአምስት አመቱ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ መጨረሻ ላይ እቅድ የተያዘ በመሆኑ ሽፋኑ የተሟላ ሊሆን አለመቻሉን ገልጸዋል፡፡

62. ይህም ፕላኖች በሚተገበሩበት ጊዜ በተለያዩ ምክንያቶች ከፍተኛ የሆነ ህገወጥነት እንዲስፋፋ የከተሞች ፕላን በተሟላ ሁኔታ እንዳይተገበርና የታለመውም ውጤት እንዳይገኝ ምክንያት ይሆናል፡፡

63. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት ክልሎች ውስጥ በሀረሪና በጅማ ለኃላፊዎች በቀረበው መጠይቅና በመስክ ጉብኝት ወቅት እንደታየው እንዳንድ የከተማ ቦታዎች ለመኖሪያ ሥፍራ ታቅዶ የነበረው ወደ ንግድ ሥፍራ እንደተቀየረ፡ መንገዶች፤ የአረንጓዴ ቦታዎችና ሌሎችም በትክክል በፕላኑ ላይ በተቀመጠላቸው ቦታ እንዳልተሰሩና ለሌላ አገልግሎት መዋላቸውን ለመረዳት ተችሏል፡፡

64. በተጨማሪም በናሙና በታዩት በጅማ ፤በድሬደዋና በሀረር ከተሞች  በአካባቢ ልማት ፕላን ላይ ሰፍሮ ከሚገኘው ውጭ በግለሰቦችም ሆነ በተለያዩ ሴክተሮች የፕላን ጥሰት መፈጸሙን ለመመልከት ተችሏል፡፡ጥሰቱ ከተፈጸመባቸው ውስጥ፡-

**በድሬዳዋ ከተማ፤**

የድሬደዋ ሪፈራል ሆስፒታል ግማሽ ለደን በተከለለና ግማሽ መዝናኛ በነበረ ቦታ የተሰራ መሆኑ፡፡

**በሀረር ከተማ፤**

- በደከር ሰፈ ወረዳ የደን ቦታ የነበረ የጥቃቅንና አነስተኛ  ኢንተርፕራይዝ ልማት ኤጀንሲ የምግብ ዝግጅት ወርክ ሾፕ (ባለ ሁለት ፎቅ) ግንባታ፣
- በደከር ሰፈ ወረዳ የደን ቦታ የነበረ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተር ፕራይዝ ልማት ኤጀንሲ ተጨማሪ የምግብ ዝግጅት ወርክ ሾፕ(ባለ ሁለት ፎቅ) ግንባታ፣
- በሐማሬሳ (ሀኪም) የደን ቦታ የነበረ ቁጥር አንድ እና ሁለት የልብስ ስፌት ወርክ ሾፕ(ባለ አራት ፎቅ)፣
- በሐማሬሳ (ሀኪም) የደን ቦታ የነበረ ተጨማሪ የልብስ ስፌት ወርክ ሾፕ ግንባታ (ባለ አራት ፎቅ)፣
- በሀማሬሳ ለመኖሪያ  የነበረ ቦታ የልብስ ስፌት ወርክ ሾፕ ግንባታ (ባለ አራት ፎቅ)፣
- ቀበሌ 13 መምህራን ማሰልጠኛ ፊት ለፊት ለመኖሪያ የነበረ የውሀ ልማት ቢሮ ግንባታ፣
- ቀይ መስቀል ፊት ለፊት ለመኖሪያ የነበረ የመገናኛ ብዙሀን ቢሮ ግንባታ (ባለ 4 ፎቅ)

**በጅማ ከተማ፤**

- በመርካቶ አካባቢ የሚገኘው በተለምዶ ዶሮ ተራ የሚባለው  ሰፈር በአዲሱ የከተማ ፕላን መሰረት  ለመኪና ማቆሚያ ተብሎ የታቀደ ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ የተለያዩ የንግድ ሱቆች የተሰሩበት መሆኑ፤
- በእስቴዲየም በስተጀርባ በአዌቱ ወንዝ ዳር፤ በበቾ ቦሬ ቀበሌ ዶሎሎ ወንዝ ላይ ከድልድዩ በላይኛውና በታችኛው ቦታዎች ላይ በጥቃቅንና አነስተኛ በተደራጁና በግለሰቦች የመኪና ማጠቢያ (ላቫጆ) ተይዞ እየሰሩበት ሲሆን በፕላኑ መሰረት ግን ለበፈር ዞን ተብሎ የታቀደ  መሆኑ፡፡
- ለበፈር ዞን የታቀደው በመርካቶ አካባቢ አርማታ በሚባለው ቦታ አዊቱ ወንዝ በበቾ ድልድይ ዳር በግራና ቀኝ በኩል ለንግድ እና ለመኖሪያ የሚያገለግሉ ቤቶች ወንዙን ተከትለው በቅርበት የተሰሩና አገልግሎት እየሰጡ መሆናቸው ነገር ግን ከዚህ በፊት

በቦታው ላይ የወንዝ ሙላት ባስከተለው አደጋ ብዙዎቹ ንብረት ላይ ጉዳት መድረሱ ታውቋል፡፡ ሌሎች ዝርዝሮች በአባሪ 2 ተያይዘዋል፡፡

65. ስለጉዳዩ በናሙና የታዩት የድሬዳዋ፣ የሐረር፣ እና የጅማ ከተሞች የሚመለከታቸው ኃላፊዎች ተጠይቀው ፕላን ዝግጅትና ትግባራ ላይ ለተከሰተው ጥሰት ምክንያት ምላሽ አልሰጡም፡፡

66. ፕላን ዝግጅትና ትግበራ ላይ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በተደረገው ክትትልና ቁጥጥር መሰረት በታዩት ክፍተቶች ላይ እርምጃ ስለመወሰዱ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ መረጃ አልቀረበም፡፡

67. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው የክትትልና የግምገማ ሥራ መጋቢት 2006 ዓ.ም. በጸደቀው የከተማ ፕላን ዝግጅትና ትግበራ ስትራቴጂ መሰረት በቀጣይ ተጠናክሮ እንደሚሰራ ገልጸዋል፡፡

68. ቁጥጥርና ክትትሉ ተጠናክሮ እርምጃ የማይወሰድ ከሆነ የፕላን መሻሻል እና ለውጥ በየጊዜው የሚደረግ የማያቋርጥ ክስተት ስለሆነ በከተማ ፕላኑ ላይ የተመለከተው የመሬት አጠቃቀም ስርዓት እንዲዛባ የሚያደረግና ህገ ወጥ የመሬት ወረራ እንዲስፋፋም መንገድ የሚፈጥር ይሆናል፡፡

## የከተማ ፕላን ዝግጅትና አፈፃፀም የክትትልና የግምገማ ማንዋልና መስፈርትን በተመለከተ

69. በአገሪቱ ውስጥ ላሉ ከተሞች የሚዘጋጁ የከተማ ፕላን ዝግጅትና አፈፃፀም በከተማ ፕላን አዋጅ ቁጥር 574/2000 መሰረት ስለመሆኑ ለመከታተልና ለመገምገም የሚያስችል የመገምገሚያ መስፈርትና ማንዋል ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ በመስፈርቱም መሰረት በየከተሞቹ የሚሰሩት ፕላኖች ሊገመገሙ ይገባል፡፡

70. ይሁን እንጂ ከሚኒስትር መ/ቤቱ በአገሪቱ ውስጥ ለሚገኙ ከተሞች በተለያዩ አካላት የተሰሩትን የከተማ ፕላኖች አፈጻጸም አስመልክቶ ክትትልና ግምገማ ለማድረግ የሚያስችል የተዘጋጀ መስፈርትም ሆነ ማንዋል አለመኖሩ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

71. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መላሽ በተዘጋጁ ዝርዝር ቼክ ሊስቶች መሰረት የክትትልና ግምገማ ሥራዎች እየተከናወኑ እንደሚገኙና በፌደራል ደረጃም ወጥ የሆነ ማንዋል ተዘጋጅቶ መጽደቅ ብቻ እንደሚቀረው ገልጸዋል፡፡

72. መመሪያና መስፈረት ሳይኖር ፕላን ከዝግጅቱ ጅምሮ እስከ አፈጻጸሙ ድረስ ያለውን አሰራር ባለሙያዎች እራሳቸው ባዘጋጁት መስፈርት የሚገመግሙ ከሆነ ተቋማዊ የሆነ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት እንዳይኖር ያደርገዋል፡፡

## የክትትልና የግምገማ ሪፖርት ግበረ-መልስና የተወሰደ እርምጃን በተመለከተ

73. የሚኒስቴር መ/ቤቱ በመላው አገሪቱ የሚዘጋጁት የከተማ ፕላን ዝግጅትና አፈጻጸም በከተማ ፕላን አዋጅ ቁጥር 574/2000 መሠረት ስለመሆኑ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ ለዚህም በክልሎችና ቻርተር ባለው ከተማ የክትትልና የግምገማ ሥራ በማከናወን ድጋፍ ሊያደርግና እና ግበረ-መልስ ሊሰጥ ይገባል፡፡ በተሠጠው ግበረ መልስ መሰረትም የእርምትና የማስተካከያ እርምጃ መሰዱንም ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

74. በኦዲቱ ወቅት ግምገማ የተከናወነ መሆኑን ነገር ግን በግምገማ ወቅት በርካታ ግኝቶች የተገኙ ቢሆንም እነዚህ ግኝቶች ላይ የእርምት ርምጃ ያልተወሰደ ሲሆን ስህተቶቹ በነበሩበት ሁኔታ ቀጥለው መገኘታቸውን እና ተመሳሳይ የሆኑ ስህተቶች እንደገና እየተደገሙ መሆኑን በመስክ ጉብኝት ወቅት በስፍራው በመገኘት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

75. ስለጉዳዩ የጅማ፣ የድሬደዋና፣የሀረር ከተሞች ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ክትትልና ግምገማ የሚከናወን ቢሆንም የግምገማው ግብረመልስ ሪፖርት እንደማይደርሳቸው ገልጸዋል፡፡

76. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው የከተማ ፕላንና መሰረታዊ የከተማ ነክ መረጃዎች በተመለከተ ጉዳዩን ትኩረት ሰጥቶ የአሰራር ስርዓቶችን በመዘርጋት ላይ እንደሆኑ፣ የከተማ ፕላን ዝግጅትና የአፈጻጸም ክትትል፣ ግምገማና ግበረ መልስ ጋር በተያያዘ ወጥ የሆነ የመረጃ አያያዝ፣ አደረጃጀትና የልውውጥ ስርዓት በከተማ ፕላን ዝግጅትና ትግበራ ስትራቴጂ እንደ አቢይ ጉዳይ የተካተተ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ የከተማ ፕላንን የሚመለከቱ ሁሉንም መረጃዎች በማሰባሰብና በማደራጀት ለተጠቃሚ አካላት የማድረሱ ሥራ በከፊል እየተሰራ ቢሆንም በቂ ባለመሆኑ በቀጣይ ተጠናክሮ እንደሚሰራበት ገልጸዋል፡፡

77. ግምገማና ክትትል ከተደረገ በኋላ የግብረመልስ ለክልሎቹና ለከተሞች ደርሰው የማስተካከያና የዕርምት እርምጃ እንዲወስዱ ካልተደረገ ችግሮቹ እንደነበሩ እንዲቀጥሉ ከማድረጉም በላይ ለክትትልና ግምገማ ለማድረግ የወጣው ሀብትና ጊዜ በከንቱ እንዲባክን ያደርጋል፡፡

## 2.4 የከተማ ፕላን አፈጻጸምን በተመለከተ ቅንጅታዊ አሰራር እና የመረጃ ልውውጥ ተግባር ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና እና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ፤

### ከከተማ ፕላን ምንጭ፤ ዝግጅት እና አፈጻጸም ጋር የተያያዙ መረጃዎች አያያዝን በተመለከተ

78. ከከተማ ፕላን ጋር የተያያዙ በየጊዜው የሚመጣውን ተለዋዋጭ የከተማ ዕድገት ባህሪ ያገናዘበ የጥናት ሰነድና ማስረጃዎች ተደራጅተው መያዝ አለባቸው፡፡ በተጨማሪም በሚኒስቴር መ/ቤቱና የሚመለከታቸው የክልል አካላት ለከተማ ፕላን ምንጭና ዝግጅት የሚያገለግሉ መረጃዎች ሊያሰባሰቡ፣ ሊያደራጁና በማጠናቀር ሊያዙ ይገባል፡፡የጥናቱ ማስረጃዎች በየከተማው ማዘጋጃ ቤት እንዲቀመጡ ሊደረግ ይገባል፡፡

79. የተሰበሰቡትም መረጃዎች ሥራ ላይ እንዲውሉ ለሚመለከታቸው አካላት የሚደርስበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ስለከተማ ፕላን ዝግጅት እና አተገባበር ባለድርሻ አካላት (በተለይም የመሠረተ ልማት አቅራቢዎች) መንግሥታዊም ሆነ መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት ጋር ሚኒስቴር መ/ቤቱ፣ ክልሎችና ከተሞች የጋራ መግባቢያ ሰነድ ሊፈራረሙና ተግባራዊ ሊደርጉት ይገባል፡፡

80. ይሁን እንጂ በኦዲት ወቅት በናሙና የመስክ ጉብኝት በተደረገባቸው የጅማ፣ የድሬዳዋና የሀረር ከተሞች የከተማ ፕላን የማመንጨት ሂደት ቃለ ጉባዔ፣ የመሬት አጠቃቀም ጥናት፤የመሰረተ ልማት እቅድ፣ የክትትልና ግብረ መልስ ሪፖርቶች፣ የረቂቅ ፕላኖች ውይይት ቃለ ጉባዔ እና ሌሎችም ማስረጃዎችን ከተለያዩ ቢሮዎቹ እንዲቀርቡ ተጠይቀው ሊቀርቡ አልቻሉም፡፡

81. በተጨማሪም በሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ በክልል የከተማ ልማት ቢሮዎች ማስረጃዎቹንም በኃላፊነት በማሰባሰብ ለሌሎች አካላት እንዲደርሱ አለማድረጋቸው ታውቋል፡ የመረጃዎች የልውውጥ ሥርዓትም ያልተዘረጋና የከተማ ፕላን ዝግጅትና አተገባባር ላይ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ካላቸው ባለድርሻ አካላት (የመሠረተ ልማት አቅራቢዎችን ጨምሮ) ጋር የጋራ መግባቢያ ሰነድ የሚኒስቴር መ/ቤቱ፣ ክልሎችና የከተማ መስተዳድሮች ያልተፈራረሙ መሆኑ ታውቋል፡፡

82. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ለሁለተኛ ጊዜ በሰጡት የነባራዊ ሁኔታ አስተያየት እና በተያያዘው አባሪ የተጠየቀው ማስረጃን የማሰባሰብና የማጠናቀር ሥርዓት መዘርጋቱን የሚያሳይ ማሰረጃ ሲሆን የቀረበው የ2005 የፕላን ዝግጅት እቅድ አፈጻጸምና የ2006 የእቅድ ዝግጅት ግብረ መልስ ሲሆን፤ ቢሆንም የከተማ ፕላንን

የሚመለከቱ ሁሉንም መረጃዎች በማሰባሰብና በማደራጀት ለተጠቃሚ አካላት የማድረሱ ሥራ በከፊል እየተሰራ ቢሆንም በቂ ባለመሆኑ በቀጣይ ተጠናክሮ እንደሚሰራበት ገልጸዋል፡፡

83. የከተማ ፕላንና መሰረታዊ የከተማ ነክ መረጃዎች ፤የከተማ ፕላን ዝግጅት የአፈጻጸም የክትትል፤ግምገማና ግብረመልስ ወጥ የሆነ የመረጃ አያያዝ፤አደረጃጀትና የልውውጥ ሥርዓት በመዘርጋት ረገድ ክፍተት ያለ በመሆኑ በጸደቀው የከተማ ፕላን ዝግጅትና ትግበራ ስትራቴጂ ውስጥ እንደ አንድ አብይ ጉዳይ የተካተተ በመሆኑ በቀጣይ ተጠናክሮ ይቀጥላል በማለት ገልጸዋል፡፡

84. የክትትልና ግምገማም ሪፖርት በተመለከተ በ2005 የከተማ ልማት፤ቤቶች እና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በጅማ ከተማ ላይ በካሄደው የፕላን አፈጻጸም ግምግማ እና ግብረ-መልስ ሪፖርት መሠረት ጉላኪቶ (አየር መንገድ መሄጃ) ላይ ለደን (Forest) የታቀደው ወደ ሬድዮ ጣቢያ የመሬት አጠቃቀም ለውጥ ተደርጓል ተብሎ ሪፖርት የቀረበ ቢሆንም፤ ሬድዮ ፋና ከመጀመሪያ ጀምሮ በቤተመንግሥት ውስጥ ጊቤ አዳራሽ በጊዜያዊነት ተሰጥቶ እየተጠቀመበት የሚገኝ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ጉምሩክ ጊቢ ውስጥ ለአስተዳደር (Administration) ታቅዶ የነበረውን ቦታ ለሬድዮ ጣብያው ለመስጠት በሂደት ላይ የሚገኝ መሆኑ፣ በተጨማሪም በበቾ ቦሬ ቀበሌ ቴክኒክ ሰፈር መወዳ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት አጠገብ ማንፋክቸሪንግ የነበረው ቦታ ወደ ፊዚዮቴራፒና ሪሃብሊቴሽን ክሊኒክ ተለውጠዋል ተብሎ ሪፖርት ቢቀርብም የኦዲት ቡድኑ በመስክ ጉብኝት ወቅት ባደረገው ማጣራት በፕላኑ መሠረት ተሰርቶ ተገኝቷል፡፡ ይህም የሚያመለክተው ክትትልና ግምገማ ለማድረግም የተሟላ ማስረጃ እንደማይገኝና የሚቀርበውም ሪፖርት ጉድለት እንዲኖረው የሚያደርግ መሆኑን ነው፡፡

85. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው የሚመለከታቸውን አካላት በማሳተፍ በፌዴራል ደረጃ በመጋቢት 2006 የጸደቀው የተቀናጀ የመሰረት ልማት አቅርቦት ስትራቴጂና ስልት በተሟላ መልኩ ተግባራዊ ሲሆን ችግሩን እንደሚቀርፌው ገልጸዋል፡፡

86. የከተማ ፕላንና የመሠረታዊ ከተማ ነክ መረጃዎች፤ የከተማ ፕላን ዝግጅት የአፈጻጸም የክትትል፣ ግምገማና ግብረ-መልስ፣ የተካሄዱ ጥናትቶች በሥርዓት የሚደራጁበት እና ለተጠቃሚዎች አመቺ የሚሆኑበት ወጥ የሆነ የመረጃ አያያዝ፣ አደረጃጀትና የልውውጥ ስርዓት አለመኖር፣ የፕላን ዝግጅትና አፈጻጸም ሥራ በአግባቡ መምራትንና መከታተልን እና የከተሞችን ዘላቂ ልማት ለማምጣት የሚያስችል ፖሊሲ ማሻሻያ አዳጋች ያደርገዋል፡፡

# ክፍል ሦስት

## መደምደሚያ

87. የከተማ ፕላን ምንጭ፣ ዝግጅትና እና አፈጻጸም ኢኮኖሚያዊ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ መከናወኑን እና የታሰበውን ዓላማ ለማሳካት የተቻለ መሆኑን በተመለከተ የሚከተሉት የአሰራር ግድፈቶች እና ክፍተቶች ተገኝተዋል፡፡

- ❖ በአዋጅ ቁጥር 574/2000 መሰረት በአገር አቀፍ ደረጃ ብሔራዊ የከተማ ልማት አቅድ (National Urban development scheme) አለመዘጋጀቱ፣
- ❖ ብሔራዊ የከተማ ልማት ዕቅድ ባለመዘጋጀቱ ክልላዊ የከተማ ልማት ፕላን እቅድ አለመዘጋጀቱ
- ❖ በናሙና በታዩት ከተሞች የከተሞች ፕላን በሚመነጭበትና በሚዘጋጅበት ወቅት የመሰረተ ልማት አቅራቢዎች አስተያየት በማካተት ያልተዘጋጀ መሆኑ እና የተዘጋጀው ፕላን ግልጽነትና ተጠያቂነት በሚያሰፍን መልኩ ሁሉም ድርሻውን እንዲወጣ ለማድረግ እና የከተሞቹ ነዋሪዎች ፍላጎት መካተቱና ግንዛቤ እንዲይዙ የተዘጋጁት የከተማ ፕላኖች ከመጽደቃቸው በፊት የከተማው ህዝብና ባለድርሻ አካላት እንዲወያዩበት አለመደረጉ፡፡
- ❖ በከተሞች ፕላን ሲዘጋጅ የአረንጓዴ አካባቢ ስፍራ እና የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች በግልጽ ተለይተው ያልተቀመጡ እና የከተሞች መልሶ ማልማት እቅድም ተዘጋጅቶ ተግባራዊ አለመደረጉ
- ❖ በፕላን ትግበራ ወቅት ለውጥ የተደረገባቸው ቦታዎች የፕላን ክለሳ በሚደረግበት ወቅት በአካባቢ የልማት ፕላን (Local Development Plan) ላይ እንዲሰፍሩና በሚመለከተው አካል እንዲጸድቁ ያልተደረገ መሆኑ፡፡
- ❖ ፕላንን በሚመለከት ለሚደረግ የቴክኒክና የአቅም ግንባታ ድጋፍ ለመስጠት የተዘጋጀው የአሰራር ማንዋል የሚመለከታቸውን አካላት ያላሳተፈና አስተያየት እንዲሰጡበት ያልተደረገ መሆኑ፣
- ❖ ለከተማ ፕላን ዝግጅትና አፈጻጸም የተዘጋጁ የጥናት ሰነዶች ተግባራዊ እንዲደረጉ ለሚመለከታቸው አስፈጻሚ አካላት እንዲደርሳቸው አለመደረጉ፣ ጥናቱ በደረሳቸው ከተሞችም ጥናቶቹም በትክክል ሥራ ላይ የዋሉ ለመሆኑ ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ ፡፡

- ❖ በአገሪቱ ውስጥ ላሉ ከተሞች የሚዘጋጁ የከተማ ፕላን ዝግጅትና አፈፃፀም በከተማ ፕላን አዋጅ ቁጥር 574/2000 መሰረት ስለመሆኑ ለመከታተልና ለመገምገም የሚያስችል የመገምገሚያ መስፈርትና ማንዋል ያልተዘጋጀ መሆኑ፣
- ❖ የከተማ ፕላን በሚተገበርበት ወቅት የፕላን ጥሰት እንዳይኖር ክትትልና ቁጥጥር የማይደረግ መሆኑ፡፡
- ❖ ፕላን በተዘጋጀላቸው ከተሞች ፕላን ትግበራ ወቅት የፕላን ጥሰት የተፈጸመ መሆኑና በፕላኑ ላይ ከተመለከተው ውጭ ለሚፈጸም ጥሰት በወቅቱ እርምጃ የማይወሰድ መሆኑ፣
- ❖ በፕላን ዝግጅትና አፈጻጸም በሚኒስቴር መ/ቤቱ ክትትልና ግምገማ ቢደረግም ግበረ መልሱ ለከተሞቹ እንዲደርሳቸው የማይደረግ መሆኑ
- ❖ ለከተማ ፕላን ምንጭና ዝግጅት የሚያገለግሉ መረጃዎች በማሰባሰብና በማደራጀት ተጠናቅረው እንዲያዙ ያልተደረገ መሆኑ ፡፡
- ❖ የከተማ ፕላን የሚመለከቱ መረጃዎች የተለያዩ አካላት እንዲጠቀሙበት ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፣
- ❖ ስለከተማ ፕላን ዝግጅት እና አተገባበር ባለድርሻ አካላት (በተለይም የመሠረተ ልማት አቅራቢዎች) ጋር ሚኒስቴር መ/ቤቱ፣ ክልሎችና ከተሞች የጋራ መግባቢያ ሰነድ ያልተፈራረሙ መሆኑ

ታውቋል፡፡

ስለሆነም በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን የአሰራር ግድፈቶችና ድክመቶች ሊያሻሽሉ ይችላሉ ተብለው የታመነባቸው የማሻሻያ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡

# ክፍል አራት

# የማሻሻያ ሀሳቦች

88. የከተሞችን ፕላን ምንጭ እና ዝግጅት ቀልጣፋና እና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ፤

- አዋጅ ቁጥር 574/2000 ተግባራዊ ለማድረግ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመለከታቸውን የፌዴራልና የክልል አካላት በማሳተፍ ብሔራዊ የከተማ ልማት አቅድ (National Urban development scheme) ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡ ይህንንዕቅድን መሰረት በማድረግም ክልሎች ክልላዊ የከተማ ልማት ዕቅድና ለእያንዳንዱ ከተማ የአካበቢ ልማት ዕቅድ (Local Development Plan) ሊያዘጋጁ ይገባል፡፡
- ፕላኑም በሚዘጋጅበት ጊዜም አገር አቀፍ የልማት ስትራቴጂና ዕቅድ ላይ ሊመሰረትና የሚመለከታቸውን የፌዴራል እና የክልል አካላትን ሊያሳትፍ ይገባል፡፡
- ብሔራዊ፣ ክልላዊና የከተሞች ፕላን በሚመነጭበትና በሚዘጋጅበት ወቅት የመሰረተ ልማት አቅራቢዎችና የሕዝብ አስተያየት ሊካተትና ፕላኑ ተዘጋጅቶ ከመጽደቁ በፊት የከተሞቹ ነዋሪዎችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት አስተያየት እንዲሰጡበት ሊደረግ ይገባል፡፡ ፕላን ትገበራው ላይ ድርሻ ያላቸው አካላት ኃላፊነታቸውና ግዴታቸውን ግልጽነትና ተጠያቂነት ባለው መልኩ ተግልጸላቸው ተግባራዊ የሚያደርጉበት መልኩ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡
- የከተሞች ፕላን ሲዘጋጅ ምቹ የመኖሪያና የሥራ አካባቢ ለመፍጠር የአረንጓዴ አካባቢ ስፍራ እና የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች በግልጽ ተለይተው ሊቀመጡና በፕላኑ መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- የከተሞች የአካባቢ ልማት የመጨረሻ ረቂቅ ፕላኖች በየከተሞቹ ምክር ቤቶች /በሚመለከተው አካል ጸድቀው ተግባራዊ ሊደረጉ እና ለሚመለከታቸው የክልል ወይም የፌዴራል አካላት በወቅቱ እንዲደርሱ ሊደረግ ይገባል፡፡
- በፕላን ትግበራ ወቅት ለውጥ የተደረገባቸው ቦታዎች በአካባቢ የልማት ፕላን (Local Development Plan) ክለሳ በሚደረግበት ወቅት በፕላኑ ላይ እንዲሰፍሩና በሚመለከተው አካል እንዲጸድቁ ሊደረግ ይገባል፡፡
- በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተዘጋጀው ፕላንን በሚመለከት ለሚደረግ የቴክኒክና የአቅም ግንባታ ድጋፍ የአሰራር ማንዋል በሚመለከተው አካል ጸድቆ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

89. የከተማ ፕላንን በሚመለከት የሚደረገው የቴክኒክ እና የአቅም ግንባታ ድጋፍ ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና እና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ፤

- ❖ ለከተማ ፕላን ዝግጅትና አፈጻጸም የሚጠኑ ጥናቶች ተግባራዊ እንዲደረጉ ለሚመለከታቸው አስፈጻሚ አካላት እንዲደርሳቸው ሊደረግ፣ ከተሞቹም ጥናቶቹን ተግባራዊ ሊያደርጉት እና ጥናቶቹም በትክክል ሥራ ላይ የዋሉ ለመሆኑ ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ❖ በአገሪቱ ውስጥ ላሉ ከተሞች የሚዘጋጁ የከተማ ፕላን ዝግጅትና አፈፃፀም በከተማ ፕላን አዋጅ ቁጥር 574/2000 መሰረት ስለመሆኑ ለመከታተልና ለመገምገም የሚያስችል የመገምገሚያ መስፈርትና ማንዋል ሊዘጋጅና በመስፈርቱም መሰረት በየከተሞቹ የሚሰሩት ፕላኖች ሊገመገሙ ይገባል፡፡
- ❖ የከተማ ፕላን ትግበራ ወቅት በፕላኑ መሠረት ተግባራዊ ሊደረግና በሚተገበርበት ወቅት የፕላን ጥሰት እንዳይኖር ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

90. የከተሞች ፕላን አፈጻጸም የቁጥጥር፣ ክትትልና ግምገማ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ

- ❖ የከተማ ፕላን በሚተገበርበት ወቅት የፕላን ጥሰት እንዳይኖር ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡ በፕላኑ ላይ ከተመለከተው ውጭ ለሚፈጸም ጥሰት በወቅቱ እርምጃ ሊወሰድ የሚስችል ግልጽነትና ተጠያቂነት የሚያሰፍን የአሰራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ ሚኒስቴር /ቤቱም ክልሎቹን ለማገዝ የሚያደርገውን የድጋፍና የክትትል ሥርዓት ሊጠናከር ይገባል፡፡
- ❖ በፕላን ዝግጅትና አፈጻጸም በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚደረገው የክትትልና ግምገማ ተጠናቅሮ ሊቀጥልና ግበረ መልስ ለከተሞቹ ሊደርሳቸውና በግብረ መልሱ መሠረት እርምጃ ስለመወሰዱ ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

91. የከተማ ፕላን አፈጻጸምን በተመለከተ ቅንጅታዊ አሰራር እና የመረጃ ልውወጥ ተግባር ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና እና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ፤

- ❖ በሚኒስቴር መ/ቤቱና በክልል በሚመለከታቸው አካላት ለከተማ ፕላን ምንጭና ዝግጅት የሚያገለግሉ መረጃዎች ሊሰባሰቡ፣ ሊደራጁና ተጠናቅረው ሊያዙ ይገባል፡፡የጥናቱ ማስረጃዎች በከተማው ማዘጋጃ ቤት እንዲቀመጡ ሊደረግ ይገባል፡፡

- ❖ የከተማ ፕላን የሚመለከቱ መረጃዎች የተለያዩ አካላት እንዲጠቀሙበት፣ ለልምድ ልውውጥ ለጥናትና ለምርምር ጭምር እንዲያግዙ ለማድረግ የሚያስችል የመረጃ አያያዝና አደረጃጀት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ❖ ስለከተማ ፕላን ዝግጅት እና አተገባበር ባለድርሻ አካላት (በተለይም የመሠረተ ልማት አቅራቢዎች) ጋር ሚኒስቴር መ/ቤቱ፣ ክልሎችና ከተሞች የጋራ መግባቢያ ሰነድ ሊፈራረሙና ተግባራዊ ሊያደርጉት ይገባል፡፡

92. በአጠቃላይ የከተማ ፕላን ምንጭ ዝግጅት እና አፈጻጸም የከተማ ፕላንን በሚመለከት የሚደረገው የቴክኒክ እና የአቅም ግንባታ ድጋፍ ኢኮኖሚያዊ፣ቀልጣፋና እና ውጤታማ መሆኑ፤ ከተማን መልሶ የማልማት እድሳትን ማከናወንና መምራት በአካባቢ ማእቀፍ ላይ ተመስርቶ በበቂ ምክንያት የተደገፈና የታቀደ መሆኑ ፤ የከተማ ፕላን ዝግጅትና አፈጻጸም ላይ የቴክኒክና አቅም ግንባታ ድጋፍ መደረጉ፤ የከተሞች ፕላን አፈጻጸም የቁጥጥር፣ ክትትልና ግምገማ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉ፤ እንደዚሁም የከተማ ፕላን አፈጻጸምን በተመለከተ ቅንጅታዊ አሰራር እና የመረጃ ልውወጥ ስርዓት ተዘርገቶ ተግባራዊ መደረጉ የከተማ ልማት፤ ቤቶች እና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴርንም ሆነ ሌሎች የከተማ ፕላን የሚያዘጋጁና በከተማ ፕላን የሚጠቀሙ የመንግሥት አካልም ሆነ የግል ባለሀብቶች በተቀላጠፈና ህጋዊ በሆነ ሁኔታ የልማት ሥራቸውን እንዲያከናውኑ ያግዛቸዋል፡፡ ይህም ስራ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከፕላን ዝግጅትና አፈጻጸም ጋር ግንኙነት ያላቸውን የፌዴራል እና የክልል አስፈጻሚ አካላትን የማስተባበርና ንቁ ተሳትፎ ይጠይቃል፡፡

93. በዚህ ሪፖርት ከተገለጹት ግኝቶች፣ መደምደሚያዎች እና የማሻሻያ ሀሳቦች ውስጥ ሚኒስቴር መ/ቤቱን በቀጥታ የማይመለከቱ ቢኖሩም ሚኒስቴር መ/ቤቱን በዋነኛነት የተቋቋመበትን ዓላማና ኃላፊነት ለመወጣት ስለሚያግዘው በተጠቀሱት ችግሮች ላይ የተሰጡትን የማሻሻያ ሀሳቦች ለሚመለከታቸው አካላት በማሳወቅ ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ ማመቻቸት ይጠበቅበታል፡፡

በመጨረሻም የከተማ ልማት፤ቤቶች እና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የሥራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች በኦዲቱ ወቅት መረጃ የተሰበሰበባቸው የፌዴራል እና የክልል መ/ቤቶች ኃላፊዎች እና ሠራተኞች ስላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

# አባሪ 1፡ የኦዲት የትኩረት አቅጣጫና የኦዲት መመዘኛ መስፈርት

| *የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ* (Audit Issues) | *የኦዲት መመዘኛ መስፈርት Evaluative Criteria* |
|---|---|
| *የከተሞችን ፕላን ምንጭ እና ዝግጅት ቀልጣፋና እና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ፤* | 1. *የከተማ ፕላን የማመንጨት ሂደት ሊጀመር የሚችለው በሚመለከታቸው ቻርተር ባላቸው ከተሞችና የከተማ አስተዳደሮች፤ የክልልና የፌዴራል አካላት አማካኝነት ሊሆን ይገባል፡፡* |
| | 2. *ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው የፌዴራል መንግሥት አካላት ጋር በመተባበር የሃገር አቀፍ የልማት ቀጠና እና የልማት ማዕከላትን ታሳቢ ያደረገ ብሔራዊ የከተማ ልማት አቅድ* (National Urban development scheme) *ሊዘጋጅ ይገባል፡፡* |
| | 3. *የከተሞች ፕላን ዝግጅት ከመጀመሩ አስቀድሞ የክልላዊ የከተማ ልማት ፕላን ሊዘጋጅ ይገባል፡፡* |
| | 4. *እንደየአግባቡ ከክልልና ከአገር አቀፍ የከተማ ልማት እቅዶች ጋር የተጣጣመ ከተማ አቀፍ መዋቅራዊና የአካባቢ ልማት ፕላን ሊዘጋጅ ይገባል፡፡* |
| | 5. *የከተሞች ፕላን በሚመነጭበትና በሚዘጋጅበት ወቅት የሕዝብ ተሳትፎ፤ ግልጽነትና ተጠያቂነት እንዲኖር በማድረግ የህብረተሰቡ ፍላጎት መሟላቱ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡* |
| | 6. *የከተማ ፕላን በሚዘጋጅበት ወቅት ውጤታማ የመሬት አጠቃቀምን መሰረት ያደረገ ሊሆን ይገባል፡፡* |
| | 7. *የከተማ ፕላን በሚዘጋጅበት ወቅት የከተሞች ዘላቂ ልማትን በሚያረጋግጥ ሊሆን ይገባል፡፡* |
| | 8. *በከተማ ፕላን ዝግጅት ወቅት የሚመለከተው-ማንኛውም መንግሥታዊም ሆነ መንግሥታዊ ያልሆነ አካል ሊያሳትፍ የሚችል የአሠራር ሥርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡* |
| | 9. *ከተሞች መዋቅራዊና የአካባቢያዊ ፕላኖቻቸውን ሲያዘጋጁና ሲከልሱ ወይም እንዲከለስላቸው ሲያደርጉ በመስኩ ባለሙያ ሊሆን ይገባል፡፡* |
| | 10. *የከተሞች ፕላን ከመጽደቁ በፊት የከተማው ህዝብ እንዲወያይበት ሊደረግ ይገባል፡፡* |
| | 11. *ስለ ከተሞች ፕላን ዝግጅትና ሂደቶቹ ለከተማው ህብረተሰብና ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በቅድሚያ ግንዛቤ ሊሰጣቸው ይገባል፤፤* |
| | 12. *የከተሞች መዋቅራዊና የአካባቢ ልማት የመጨረሻ ረቂቅ ፕላኖች በየከተሞቹ ምክር ቤቶች ውይይት ከተደረገባቸው በኋላ በሚመለከተው አካል ጸድቆ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡* |
| | 13. *የጸደቀው የከተማ ፕላን ለሚመለከታቸው የክልል ወይም የፌዴራል አካላት እንዲደርስ ሊደረግ ይገባል፡፡* |
| | 14. *የከተሞች መዋቅራዊና የአካባቢ ልማት የመጨረሻ ረቂቅ ፕላኖች በአዋጅ ከተደነገጉት መሠረታዊ መርሆዎች ጋር የሚጣጣም መሆኑ ከመጽደቁ በፊት ሊረጋገጥ ይገባል፡፡* |
| *የከተማ ፕላንን በሚመለከት የሚደረገው የቴክኒክ እና የአቅም ግንባታ ድጋፍ ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና እና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ፤*<br>ከተማን መልሶ የማልማት፤ እድሳትን ማከናወንና መምራት በአካባቢ ማእቀፍ ላይ ተመስርቶ በበቂ ምክንያት የተደገፈና የታቀደ መሆኑን ማረጋገጥ | 15. *ማንኛውም የጸደቀ ፕላን በሚተገበርበት ወቅት የፕላን ጥሰት እንዳይኖር ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡* |
| | 16. *የከተማ አስተዳደሮች የአስተዳደሮቻቸውን፤ የነዋሪዎቻቸውን፤ የአልሚዎቻቸውን ተነሳሽነት ተከትለው መዋቅራዊና የአካባቢ ልማት ፕላኖችን መሰረት በማድረግ እንደገና እንዲለሙና እንዲያንሰራሩ ሊያደርጉ ይገባል፡፡* |
| | 17. *ማንኛውም የጸደቀ ፕላን ጸንቶ የሚቆይበት የጊዜ ገደብ የመጠናቀቂያ ጊዜ ሲቃረብ የማሻሻል ሥራ ሊከናወን ይገባል፡፡* |
| | 18. *በሚ/ር/መ/ቤቱ ለክልል ከተሞችና ለፌዴራል መንግሥት ተጠሪ ለሆኑ ከተሞች የከተማ ፕላንን በሚመለከት የቴክኒክና የአቅም ግንባታ ድጋፍ የአሰራር ማንዋል ሊዘጋጅና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡* |
| | 19. *ክልሎች (የከተማ አሰተዳድሮች)ከተማን የማደስ ተግባር፤ በአንድ ከተማ ውስጥ የሚታዩትን የፈራረሱ፤ ያረጁ፤ የተተዉ መዋቅሮች በከፊል ወይም በሙሉ በማስወገድ ምቹ የመኖሪያና የሥራ አካባቢ ለመፍጠር እቅድ በማዘጋጀት ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ ፡* |
| | 20. *ከተማ አስተዳደሮች ከተሞችንለማደስ የፌዴራል መንግሥትን በማማከር ከክልሉ ፈቃድ ሊያገኙ ይገባል፡፡* |
| | 21. *ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፌዴራል እና በየክልሉ የሚገኙ ቻርተር ከተሞች ስለከተማ ፕላን ምንጭ፣ዝግጅት እና አፈጻጸምን በተመለከተ የልምድ ልውውጥ ለማስተላለፍ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓትበሚኒስቴር መ/ቤቱ ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡* |
| | 22. *በሚኒስቴር መ/ቤቱ የፕላን አዘገጃጀት ዘዴዎች፣ማንዋሎች፤ ስታንዳርድ እና ፕሮግራሞችን ለማዘጋጀት አስቀድሞ የክፍተት ዳሰሳ ጥናት ሊሰራ ይገባል፡፡* |
| | 23. *የከተማ ፕላን ዝግጅትና አፈጻጸም ሥራዎች በተሟሉ የአሰራር ማንዋሎች መሰረት እንዲከናወኑ የተለያዩ የጥናት ሰነዶች ሊዘጋጅና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡* |
| | 24. *የተዘጋጀው የጥናት ሰነድ በትክክል ሥራ ላይ የዋለ ለመሆኑ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡* |
| | 25. *ሚኒስቴር መ/ቤቱ የከተማ ፕላን ዝግጅትና አፈጻጸምን በተመለከተ የሥልጠና አሰጣጥ ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡* |

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት *Evaluative Criteria* |
|---|---|
| | 26. በተዘረጋው ስርዓት መሰረት የተሰጠው ስልጠና ውጤታማ መሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ |
| | 27. የከተማ አመራሮች ፕላኖችን በአግባቡ ተገንዝበው የተቀናጀ መሠረተ-ልማት ለማቅረብ የሚያስችል ዕቅድ እንዲያዘጋጁ ስልጠና ሊሰጥ እና አፈጻጸሙ ላይ ክትትል ሊደረግ ይገባል:: |
| | 28. በየክልል ከተሞች የከተማ ፕላን ዝግጅት ላይ በመሳተፍ በየጊዜው የመስክ የሥራ ላይ<br>29. ሥልጠና ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| | 30. በመንግሥት የፕላን ዝግጅት ተቋማት ለሚሠሩ ባለሙያዎች እና የግል አማካሪ ድርጅቶች የሙያ ማዳበሪያ ስልጠና ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| | 31. በፕላን ዝግጅት ለሚሳተፉ የግል አማካሪ ድርጅቶች ከፕላን ዝግጅት ጋር የተያየዘ የልምድ ልውውጥ ሥርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| የከተሞች ፕላን አፈጻጸም የቁጥጥር፣ክትትልና ግምገማ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ | 32. የከተማ ፕላን ዝግጅትና አፈፃፀም በከተማ ፕላን አዋጅ መሰረት ስለመሆኑ ለመከታተልና ለመገምገም የሚያስችል ማንዋል ሊዘጋጅ እና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 33. በከተማ ፕላን ዝግጅትና አፈፃፀም ላይ ክትትልና ግምገማ ለማድረግ እንደፕላኖቹ አይነትና ሁኔታ የመገምገሚያ መስፈርት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 34. የከተማ ፕላን ዝግጅት በከተማ ፕላን አዋጅ መሠረት ስለመሆኑ በክልሎችና ቻርተር ባላቸው ከተሞችን የክትትልና የግምገማ ሥራ በማከናወን ድጋፍ እና ግበረ-መልስ ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| | 35. የከተማ ፕላን ዝግጅትን በተመለከተ የክትትልና የግምገማ ሥራ ውጤት ለበላይ አመራር በሪፖርት ሊቀርብ እና እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ |
| | 36. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የከተማ ፕላኖች ከአዋጅ ጋር የሚጣጣሙ ስለመሆናቸው ቁጥጥርና ክትትል በማድረግ በአገሪቱ ውስጥ የተመጣጠነና የተቀናጀ የከተማ ልማት መኖሩ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ |
| | 37. የከተማ ፕላን ዝግጅትና አፈፃፀም በግምገማ ሪፖርት መሠረት የእርምት/ ማስተካከያ እርምጃ የተወሰደ ስለመሆኑ በሚ/ር መ/ቤቱ ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| የከተማ ፕላን አፈጻጸምን በተመለከተ ቅንጅታዊ አሰራር እና የመረጃ ልውወጥ ተግባር ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና እና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ፤ | 38. የከተማ ፕላን ምንጭ፤ዝግጅት እና አፈጻጸምን በተመለከተ መረጃዎችን የማሰባሰብና የማጠናቀር ሥርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 39. የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የከተማ ፕላንን የሚመለከቱ መረጃዎች፤በማሰባሰብና በማደራጀት ለሌሎች አካላት እንዲደርሱ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 40. የከተማ ፕላን ዝግጅት የአፈጻጸም የክትትል፣ ግምገማና ግብረ-መልስ ወጥ የሆነ የመረጃ አያያዝ፣ አደረጃጀትና የልውውጥ ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 41. ሚ/ር መ/ቤቱ የከተማ ፕላንና የመሠረታዊ ከተማ ነክ መረጃዎችን በማደራጀት ለሚመለከተው አካላት ለማስተላለፍ እና ለማሰራጨት የሚያስችል ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 42. ሚ/ር መ/ቤቱ በከተማ ፕላን ዝግጅት እና አተገባበር ዙርያ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የጋራ መግባቢያ ሰነድ ሊኖር እና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 43. የልማት አፈቃቀድ ደንቦችን አጠቃላይ ተፈጻሚነት በብሄራዊ ደረጃ ክትትልና ግምገማ ሊደረግ ይገባል፡፡ |

# አባሪ ሁለት

## በሐረር ከተማ በፕላኑ ላይ የተደረጉ ለውጦች

| ተ.ቁ | በመሬት አጠቃቀም እቅድ ላይ የነበረው አገልግሎት | የተደረገው የመሬት አጠቃቀም ለውጥ | አሁን ቦታውን እተጠቀመበት ያለ አካል | ቦታው የሚገኝበት ሰፈር |
|---|---|---|---|---|
| 1. | CO 1(ንግድ) | R(መኖሪያ) | ግለሰብ | ቀበሌ 18 ኖክ |
| 2. | CO1(ንግድ) | R(መኖሪያ) | ግለሰብ | ቀበሌ 18 ኖክ |
| 3. | CO1(ንግድ) | R(Residence) | ግለሰብ | ቀበሌ 18 ሚሽን አካባቢ |
| 4. | CO19(ንግድ) | CO(ንግድ) | ግለሰብ | ቀበሌ 18 ሚሽን አካባቢ |
| 5. | CO11(ንግድ) | R | ግለሰብ | ቀበሌ 18 ሚሽን አካባቢ |
| 6. | CO11(ንግድ) | R | ግለሰብ | ቀበሌ 18 ሚሽን አካባቢ |
| 7. | RE12(Real steat) | Real steat | ባለ ሐብት | ግንደ በላይ (ኮንዶሚኒየም ፊት ለፊት) |
| 8. | AD12(administration) | M(ባቢሌ ውሃ) | ድርጅቱ | ግንደ በላይ (ኮንዶሚኒየም ፊት ለፊት) |
| 9. | CO1 & T1 (commerce&transport) | R(መኖሪያ) | ግለሰብ | ቀበሌ 13 መቻሬ |
| 10. | F2(forest) | R(መኖሪያ) | ግለሰብ | ወደ ጅጅጋ መስመርና ማደያው አለፍ ብሎ |
| 11 | FOREST | R(መኖሪያ) | ግለሰብ | ደደር ቀበሌ ጅጅጋ መስመር |

## በድሬደዋ ከተማ አስተዳደር በፕላኑ ላይ የተደረጉ ለውጦች

| ተ.ቁ | በመሬት አጠቃቀም እቅድ ላይ የነበረው አገልግሎት | የተደረገው የመሬት አጠቃቀም ለውጥ | አሁን ቦታውን እተጠቀመበት ያለ አካል | ቦታው የሚገኝበት ሰፈር |
|---|---|---|---|---|
| 1. | R(MIXED use) | T1(መናኸሪያ) | ተቋራጭ | ቀበሌ 02 ጉሮ ሰፈር |
| 2. | R(Mixed use) | S(የማሪያም ወርቅ ሆስፒታል) | ግለሰብ | ቀበሌ 02 ጉሮ ሰፈር |
| 3. | F2(forest) | M(ማደያ) | ግለሰብ | ቀበሌ 02 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 4. | F2(forest) | R(መኖሪያ) | ግለሰቦች | ቀበሌ 02 |
| 5. | F2(forest) | RE(መዝናኛ) | ግለሰብ | ቀበሌ 20 |
| 6. | RE11(real steat) | M(የጫት ማህበር ) | ማህበሩ | ሰባተኛ |
| 7. | CO,S,RE,F2(commerce,service,recreation,forest) | M(ኢትዮ ቱርክ ጨርቃ ጨርቅ) | ድርጅቱ | ኢንዱስትሪ መንደር |
| 8. | R2,A2(mixed residence,Agriculture) | M(ስሚንቶ ፋብሪካ ፓይነር) | የቻይና ባለሐብት | |
| 9. | M, S73.2/ (manufacture,service) | M(ማደያ) | ግለሰብ | ቀበሌ 09 ሰፈር ሰባት |
| 10. | RE12,M(recreation,Manufacture) | S(ት/ቤት) | ት/ቤቱ | ቀበሌ 09 ሰፈር ሰባት |
| 11. | A(Agriculture) | R(መኖሪያ) | ሐጅ ሽኩራዲ ሪል ስቴት(ግለሰብ) | ቀበሌ 03 ሽንሌ መንገድ |

## በጅማ ከተማ በፕላኑ ላይ የተደረጉ ለውጦች

| ተ.ቁ | በመሬት አጠቃቀም እቅድ ላይ የነበረው አገልግሎት | የተደረገው የመሬት አጠቃቀም ለውጥ | አሁን ቦታውን እተጠቀመበት ያለ አካል | ቦታው የሚገኝበት ሰፈር |
|---|---|---|---|---|
| 1. | M/manufacture/ | R & CO (ንግድ) | ግለሰብ | ቀበሌ 07 ቦቻ ቦሬ ዳውሮ በር |
| 2. | MU/mixed use/ | S(sos school) | ተቋም | ቦሬ ቀበሌ 07 |
| 3. | AP/Air port/ | R(መኖሪያ) | ግለሰቦች | ቆፌ |
| 4. | Sport Center | R(መኖሪያ) | ግለሰቦች | ቦሬ ኤስ ኦ ኤስ ፊት ለፊት |
| 5. | CO(ንግድ) | S/ሪፈራል ሆስፒታል/ | ተቋም | ቦሬ የቦንጋ መሄጃ |
| 6. | M/Manufacture/ | R(መኖሪያ) | ግለሰብ | |
| 7. | M(Wood work) | S(መወዳ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት) | ግለሰብ | ቴክኒክ ሰፈር ቦቻ ቦሬ |
| 8. | M/Manufacture/ | S(ሪሀብሊቴሽንና ፊዚዮትራፒ ክሊኒክ) | ግለሰብ | ቦቻ ቦሬ ሰፈር |
| 9. | F/Forest/ | S(ሬዲዮ ፋና) | ተቋም | ጉላኪቶ (አየር መንገድ መሄጃ) |